# ወቅታዊ እና አንገብጋቢ ለሆኑ ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ለመስጠት፤ ለማስተማር፣ ለማረም፣ ለማስጠንቀቅ የተዘጋጀ ጥናት

**ማሳሰቢያ፡-**
**ይህ ጥናት በየዕለቱ በሚገጥሙን የህይወት ገጽታዎች ዙሪያ ላይ ያተኮረ ነው**

**March 2017**

# ጥናት አንድ
# የነፍስ ወከፍ ወይም
# የአንድ ለአንድ ወንጌል የማሰራጫ ዘዴ

## ዓላማ

ከብዙ የወንጌል ማሰራጫ መንገዶች አንዱ የሆነውን **"የነፍስ ወከፍ" ወይም** "አንድ ለአንድ" ወንጌልን ማዳረስ ነው፤ ይህንን በማወቅ የጌታን ቃል ላልሰሙት ማሰማት እንድንችል እንደገና ለማሳሰብ፤

## መግቢያ

በአዲስ ኪዳን ልዩ ልዩ ዓይነት የወንጌል ማሰራጫ ዘዴዎች እንዳሉ ግልጽ ነው። ከእነዚህ አንዱ በጅማ ወይም በማህበር ያልሆነ በግል አንድ ለአንድ ለሰዎች ወንጌል በመናገር ወደ ጌታ የማምጣት መንገድ ነው። ይህንን መንገድ ጌታ ኢየሱስ እንዲሁም ሐዋርያቱ በብዙ ተጠቅመውታል።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዝርዝር ጥናት

1. እንድርያስ ስምዖንን አመጣው፡- "41 ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ። 42 እርሱ አስቀድሞ የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና። መሢሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው። 43 ወደ ኢየሱስም አመጣው። ኢየሱስም ተመልክቶ አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ፤ አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው፤ ትርጓሜው ጴጥሮስ ማለት ነው።" (ዮሐ 1፡41-43)። በዚህ ምክንያት ስምዖን ወደ ክርስቶስ መምጣቱና ከብዙ መውደቅና መነሳት በኋላ ለብዙዎች የጌታን ቃል በድፍረት በማወጅ ብዙዎችን ወደ ህይወት ቃል እንደመለሰ የሚታወቅ ነው (ሐዋ 2:14-42)። ስለዚህ ከስምዖን ጀርባ እንድርያስ እንዳለና የነፍስ ወከፍ የወንጌል ስሪጭት አካሄድ እንደሆነ ማወቅ ጥሩ ነው።

2. ጌታችን ኢየሱስም በነፍስ ወከፍ ወንጌልን በማዳረስ ኃጢአተኞችን ወደ ራሱ ያመጣ ነበር።

ሀ. ፊልጶስን አመጣው (ዮሐ 1:44-46)፡-

ለ. ኒቆድሞስ (ዮሐ 3:1-17)፡- ይህንን የኃይማኖት ሰው ጌታ በግሉ ወደ ህይወት መራው። የህይወቱን ለውጥ በዮሐ 7:47-53 እና ዮሐ 19:38-42) እንመለከታለን።

ሐ. የሳምራዊቷን ሴት የድነት ታሪክ (ዮሐ 4:4-26)፡- ይህችን ሴት ከምድራዊ ነገር ፍላጎቷ ወደ ዘላለም ህይወት መራት። እርሷ ደግሞ ብዙዎችን ወደ ህይወት እንደመራቻቸው ዮሐ 4 ያስተምረናል።

መ. ሌሎችንም መጥቀስ ትችላላችሁ።

3. የናትናኤል የመዳኑ ታሪክ፡-ፊልጶስ ናትናኤልን ወደ ህይወት አመጣው (ዮሐ 1:47-52)።

በተጨማሪ ወደ ጌታ የመጡትን አንዳንዶችን በግል በማሳደግ የረዱአቸውም አገልጋዮች በቃሉ ብዙዎች ተጠቅሰው ይገኛሉ።

## <u>ንግግሩን እንዴት እንጀምር?</u>

የምናደርጋቸው ማንኛውም ዓይነት ነገሮች ለሰዎች ጥቅም ሆኖ ክብሩን ጌታ እግዚአብሔር ይውሰድ ካልን ማንኝውንም ንግግራችንን፣ ጨዎታዎቻችንና ተግባራችንን ወንጌልን ወደ ማሰማት መቀየር እንችላለን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደርግ እንደነበረው ፈለጉን መከተል እንችላለን። በምንሰራበትና በምንውልበት ቦታ ሁሉ ብዙ ጌታን የማያውቁ ሰዎች እንደምናገኛቸው ግልጽ ነው።

ስለ ኢኮኖሚ፣ስለ ሥራ፣ስለ ፖለቲካ፣ስለ ባህል፣ስለ ስፖርት፣ የሚያተኩሩትን ጭውውቶቻችንን የወንጌልን መልዕክት ለመናገር እንደ ዕዳሎቶ መጠቀም እንችላለን።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በጥናቱ መግቢያ መሰረት የዚህ ጥናት ዋናው ዓላማ ምንድ ነው?
2. የዮሐ 1:42-52 በማንበብ በነፍስ ወከፍ ስለ ክርስቶስ ተነግሯቸው ወደ ህይወት የመጡ እነ ማን ናቸው? ሁሉንም በዝርዝር ተወያዩ።
3. ሐዋ 2፡14-42 ጴጥሮስ ወንጌል የሰማበትን መንገድ እና የአገልግሎቱን አድማስ በማየት፤ በነፍስ ወከፍ አንድን ሰው ወደ ጌታ ማምጣት ሊኖረው የሚችለውን ውጤት ተወያዩበት?
4. ከኒቆድሞስ ወደ ጌታ መምጣት ምን እንማራለን? የሃይማኖት ሰዎችን እንዴት ወደ ጌታ የመመለስ እድል ሊኖረን እንደሚችል ተወያዩ (ዮሐ 3:1-16)
5. ክርስቶስ ሳምራዊቷን ሴት የማያውቃት ቢሆንም እንዴት እንደቀረባት ተወያዩ (ዮሐ 4)። ከዚህ ምን እንማራለን?
6. የምናደርጋቸው ማንኛውም ዓይነት ተግባራት ከወንጌል ጋር ማያያዝ እንችላለ ማለት ምን ማለት ነው? ተወያዩ። ምስክርነት ካላችሁ መስክሩ
7. ወንጌልን በግል ለመናገር ስዎችን የት የት እንደምናገኛቸው ዘርዝሩ፤ በነዚህ ስፍራዎች ወንጌል ለማካፈል ተግዳሮቶች ምንድናቸው?
8. ጌታ ወንጌልን የማካፈል ድፍረትና እድል እንዲሠጠን እኛም ለዚህ ታላቅ ተልዕኮ እንደተጠራን አውቀን እንድንኖር ዛሬ እንጸልያለን ዛሬውኑ በግል እቅድ እናውጣ።

## መደምደሚያ

ጌታ የህይወትን ቃል በጨለማ ላሉት እንድንናገር እና ወደ ብርሃን እንድናመጣቸው ልኮናል። ስለዚህም የህይወት ጥሪ ካርድ በእጃችን እንዳለ አውቀን እንድንቀሳቀስ ይገባና። በግል ሰዎችን ወደ ጌታ ህይወት መምጣትና የመጡትንም ማሳደግ አንዱ ውጤታማ ወንጌልን የማዳረስ ዘዴ ነው። በማንኛውም ቦታዎች የምናገኛቸውን ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንምራቸው እንላለን። በዚህም ምክንያት ህይወት ይድናል ጌታም ክብሩን ይቀበላል።

## ጥናት ሁለት

## ስልታዊ ዕቅድ፣ተልዕኮ፣ራዕይ፣ዓላማ እና ግብ

## የንባብ ክፍል ሉቃስ 14:28-32፣ሉቃ 4:17-19፣ ገላ 4:6 እና ሌሎችም

### ዓላማ

የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ስልታዊ እቅድ፣ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴቶች፣ ግብና ዓላማ የተሰኙትንና ተመሳሳይ የንድፈ ሀሳቦች (ፕሮገ ስያሜዎች) ጠንቅቆ በማወቅ በግል እና በቤተ ሰብ ሕይወታችንም ይሁን በቤተ ክርስቲያን በስልታዊ እቅድ መኖር እንድንችል እውቀት እንድንካፈል። በተለይም በዋናነት ከ2018-2022 ለሚተለመው የቤተ ክርስቲያናችን ስልታዊ ዕቅድ እና ከንውን ወቅት በብቁነት እንዲሳተፉ ለማገዝ

### መግቢያ

በስልታዊ እቅድ ውስጥ ያሉ ቃላቶች ማለትም ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴት፣ ግብና ዓላማ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተወራራሽነት ያላቸው የፕሮገ ተግባርን ማብራሪያና መተንተኛ ስያሜዎች ሲሆኑ በሌላ መልኩ ደግሞ ራሱን የቻለ ትርጉምና ትንታኔ አላቸው። በየዕለቱ ኑሮአችንና አካባቢያችን ስለ ተልዕኮ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ የኃይማኖት ተቋማት አዘውትረው ሲናገሩ እንሰማለን። እንደዚሁም ሁሉ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ስለ ራዕያቸውም ሆነ ግብና ዓላማቸው አበክረው ሲናገሩ እንሰማለን። የእነዚህን ስያሜዎች ፍችና ምሳሌያዊ ማብራሪያ እንደሚከተለው እናያለን።

### ምጥን ማብራሪያ ከነምሳሌው

1. ስልታዊ እቅድ (Strategic Planning)

በዚህ ጥናት መሠረት ስልታዊ እቅድ ማለት የግል የቤተ ሰብ እና የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እና ንብረት እንደ ብልሃተኛ አናጺ በእውቀትና በጥበብ መምራትን የሚያጠቃልል ጥቅል ሀረግ ነው። በብሉይ ኪዳን የማደሪያው ድንኳን የተሰራውና ኢያሱም የዘመተው በስልታዊ ዕቅድ ነበር። በአዲስ ኪዳንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል እንዲህ አለ “28 ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደ ሆነ

አስቀድሞ ተቀምጦ ኪሳራውን የማይቈጥር ማን ነው? 29 ያለዚያ መሠረቱን ቢመሠርት፥ ሊደመድመውም ቢያቅተው፥ ያዩት ሁሉ። 30 ይህ ሰው ሊሠራ ጀምሮ ሊደመድመው አቃተው ብለው ሊዘብቱበት ይጀምራሉ። 31 ወይም ሌላውን ንጉሥ በጦርነት ሊጋጠም የሚሄድ፥ ከሁለት እልፍ ጋር የሚመጣበትን በአንድ እልፍ ሊገናኝ የሚችል እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ የማያስብ ንጉሥ ማን ነው? 32 ባይሆንስ ሌላው ገና ሩቅ ሳለ መልክተኞች ልኮ ዕርቅ ይለምናል" (ሉቃስ 14:28-32)።

## 2. ተልዕኮ (Mission)

ተልዕኮ *ማንነታችንንና ለምን እንደምንኖር* ማለትም ልንፈጽመው ያለ ተግባር ምን እንደሆነ የሚያመላክት ፈር ቀያሽ መንገድ ነው። በግለሰብ፣ በተቋምና በድርጅት ደረጃም ይገለጻል። እግዚብሔር ታላቁን ተልዕኮ በማቴ 28:19 ላይ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷታል። ይህን ዋና መሰረት ባለመልቀቅ እያንዳንዱ ግለሰብ ቤተ ሰብና ቤተ ክርስቲያን ግልጽ የሆነ ተልዕኮ ሊኖረው ያስፈልጋል።

**ምሳሌ፡-**

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤ/ክርስቲያን ተልዕኮ ምዕመኗ በየዕለቱ ክርስቶስን እንዲመስሉ ወደ እግዜብሔር ማስጠጋትና ወንጌልን እያዳረሱ እግዚአብሔርን ያገለግሉ ዘንድ ማበረታታት፣ ማስታጠቅና ማሳተፍ ነው።

## 3. ራዕይ (Vision)

ሰው በንቁው አይምሮው እያለ ገሀድ ያልወጣውንና በሥጋ ዓይን ሊታይ የማይቻለውን ነገር ግን በዓይነ ሕሊና ቃኝቶና ተገንዝቦ ለመተግበር የሚጓጓለት ግልጽ የሆነ የአእምሮ ሥዕል ነው።

**በአማኞች አተረጓጎም፡-**

በሰማይ የሚካሄደውን መለኮታዊ ዕቅድና ተግባር በምድር ላይ እንዴት እንደምንፈጽም እግዚአብሔር ለኛ ድንጋጌና ምሪትን የሚሰጥበት የመገናኛ ዘዴ ነው። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር የሚያየውን ማየት ማለት ነው።

**ምሳሌ፡-**የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተ/ክርስቲያን በዳላስና አካባቢው ዘንድ በብዛትና በጥራት መደጓ ይፋ ሆኖ መንፈሳዊ ተጽዕኖን በማምጣት የምስራቹን ወንጌል ለሁሉም የማኅበረሰቡ ክፍል በጋለ ስሜትና ብቃት የምታዳርስ ሆና ማየት ነው።

## 4.ግብ (Goal)

ግብ ተልዕኮአችንንም ይሁን ራዕያችንን ለማሳካት የምናተኩርበት የሚታይና የሚለካ የመጨረሻ ውጤትን የሚጠቁም ጠቅለል ያለ የተግባር ክንውንን የሚያሳይ የስልት ወይም የፕሮጌ ስያሜ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የህይወት ግብ ነበረው (ሉቃ 4:16-19)። ሐዋርያው ጳውሎስም እንደዚህ በግልጽ ግቡን ተናግሮታል (ገላ 2:20)።

**ምሳሌ፡-**

1. የገቢ ምንጫችንን፣ የአባላትን ቁጥርና የባላደራነትን እውቀት ማሳደግ
2. የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማርና አምልኮን ተወዳጅ ማድረግ፣ ወ.ዘ.ተ

## 5.ዓላማ (Objective)

ዓላማ ግባችንን ለመጨበጥ (ለማሳካት) ዘርዘር ባለና ተንተን ባለ መልኩ እቅደን የምንፈጽመው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው። ልዩ ልዩ ንዑስ ዘርፎችንም ያጠቃልላል።

**ምሳሌ፡-**

**1. የገቢ ምንጭ**

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ባለፈው ዓመት ከሰበሰበቻው ብር $, 1000.000.00 በዚህ ዓመት ገቢዋን የቤተክርስቲያን መዕመናን ለቤተክርስቲያን የሚገባውን አስራት፣መባንና በኩራትን በሚገባ እንዲሰጡ በማስተማር፣ከልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ሽያጭም ሆነ በገንዘብ አሰባሰብ ዘዴ ተጠቅማ በ75% (2,500.000.00) ታሳድጋለች።

2. የአባላትን ቁጥር ማሳደግ

3. የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር
4. ባላደራነትን ማሳደግ
5. የአምልኮ አገልግሎት
6. ተግባቦትን ማሳደግ
7. የቤተክርስቲያን ሕንጻዎች መንከባከብና ማደስ
8. ሕብረተሰቡን ማገልገል
9. ቤተሰብን ማጠናከር

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ስልታዊ ዕቅድ ምንድ ነው?
2. የሚከተሉትን ቃላቶች ትርጉማቸውንና ጥቅማቸውን ተወያዩ

   ሀ. ተልዕኮ ለ. ራዕይ ሐ. ዓላማ መ. ግብ ሠ. እሴት
3. ሉቃ 14:28-32፣ገላ 4:6 እና ምሳ 30፡25 ስለ ስልታዊ ዕቅድ ምን ያስተምራል? ከዚህስ ጥናት ጋር ምን ይገናኛል?
4. ሉቃ 4:17-19 እና ገላ 2:20 ምን እናያለን?
5. በመግቢያው ሃሳብ መሰረት የዚህ ጥናት ዓላማ ምንድ ነው?
6. አማኝ እምነትንና እቅድን እንዴት ሊያስታርቅ ይችላል?
7. ከዛሬ ጥናት ምን እንደተረዳን እናካፍል
8. ቤተ ክርስቲያናችን ከ2018-2022 ላለው ለአምስት ዓመታት በዚህ በ2017 በማቀድ ላይ ስላለች ጌታ ውጤታማ የሆነ ራዕይ እንዲሰጣት እና የእኛንም ኃላፊነት መወጣት እንድንችል እንጸልያለን።

## መደምደሚያ

ገላ 4:6 እና ሉቃ 14:28-32 እንደሚያስተምረን እቅድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። እያንዳንዱ አማኝ፣ በተሰብም ይሁን ቤተ ክርስቲያን በእቅድ የተሞላ አገልግሎት እና ኑሮ ቢኖሩ የበለጠ ውጤታማ ፍሬ ያፈራሉ።

## **ጥናት** ሶስት

## ቁጣ

**ዓላማ**

በክርስትና ህይወት በቁጣም ሆነ ተከትለው በሚመጡት ንዴትና መራራነት በተባሉት መዘዞች ላይ ድል የምናገኝበትን መንገድ ማሳየት

**መግቢያ፡-**

ቁጣ ከውጪም ይሁን ከውስጥ በሚፈጠረው ማለትም በስሜት ህዋሳት በኩል በመግባት ወይም በሰውነታችን ውስጥ የነበረው ነገር በመቀስቀስ የሚመጣ የስሜት ለውጥ ወይም አሉታዊ መቀያየር ነው። ቁጣ የሚሰራው በስሜት ማንነት ይሁን እንጂ በሌሎችም የአካል ክፍሎች ላይ ከፉ ተጽዕኖና ጉዳት ያመጣል። በግሪክ ቋንቋ “ቁጣ” በስሎ ለመፈንዳት የቀረበ ፍራፍሬን ይመስላል ይላሉ። የቁጣ ምክንያቶች እና እውነተኝነት አንጻራዊ ቢሆኑም ለአማኞች የመጨረሻው የቁጣ መቆጣጠሪያ ዘዴው የእግዚአብሔር ቃል ነው። የሥነ ልቦና ጥናት፣ የባህል ደንቦች፣ የሀገር ህግ እና ልዩ ልዩ የሰው ሰራሽ የሀይማኖት አስተምህሮዎች ለአማኝ የቁጣ መማርያና መቀጣጠሪያ መሠረት ሊሆኑ አይችሉም። ሳይንስም ይሁን የጌታ ቃል ቁጣ በጤንነታችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለውም ያስረድል።

እግዚአብሔር ይቆጣል ነገር ግን እርሱ የሚቆጣው በኃጢአትና በውጤቱ ነው። ይህ ጥናት ትኩረት የሚሰጠው የሥጋ ፍሬ የሆነው እና አማኞች ትክክለኛ ባልሆነ መንገድና ቦታ ስለሚገልጡት መንፈሳዊ ስላልሆነው ቁጣ ነው። ቁጣ ደረጃው ይለያይ እንጂ ሁሉም ሰው አለበት። እንዴት ግን ድል ለንነሳ እንችላለን?

## ቁጣ

ቁጣ በሰው ልጆች ላይ ቀጣይነትና አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ አለው። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ልዩ ልዩ የቁጣ ዓይነቶች ይገኛሉ።

### 1. የእግዚአብሔር ቁጣ ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስሜት እንዳለው ይገልጻል። የስሜቱም መገለጫዎች ልዩ ልዩ መንገዶች ናቸው። ለምሳሌ ማዘን  አንዱ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ" ይላል (ኤፌ 4፥30)። እግዚአብሔር ደግም ይራራል (ኤር 30፥3 "አምላክህ እግዚአብሔር ምርኮህን ይመልሳል ይራራልህማል፤ አምላክህም እግዚአብሔር አንተን ከበተነበት ከአሕዛብ ሁሉ መካከል መልሶ ይሰበስብሃል" ብሎ ጌታ እንደሚራራ ይናገራል።

ሌላው ጌታ ስሜቱን በቁጣ ይገልጣል።  የእግዚአብሔር ቁጣ ሁል ጊዜም የሚገለጠው በኃጢአት እና በውጤቱ ላይ ነው። ይህ ደግሞ በብሉይ እና በአዲስ ኪዳንም የተረጋገጠ ነገር ነው። ሰይጣን ኃጢአትን እንደመሣሪያ በመጠቀም  ስዎችን በጌታ ላይ ያሳምጻል። እግዚአብሔር ደግሞ የጽድቅ መንገድ በግልጽ ለሰው ልጆች ስለገለጸ ሰዎች በዓመጽ ወይም ባለመታዘዝ ከቆዩ  ቁጣው ይነዳል። ስለዚህ በሰዎችና በሌሎች ተፈጥሮ ሁሉ ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣ የእግዚአብሔር ቁጣ ይገለጣል። በኖህ እና በሎጥ ጊዜ የነበረው የእግዚአብሔር ቁጣ ተፈጥሮን ሁሉ የነካ ነበር። በመጨረሻ ዘመንም የእግዚአብሔር ቁጣ በማያምኑት ሁሉ ላይ እንደሚገለጥ ቃሉ ያስተምረናል። ከኃጢዓት "የተነሣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ" ኤፌ 5፡16። "ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል" (ሮሜ 2፥8 )። የሰው ልጆች ሊቀጣ የሚችለው በኃጢአት ምክንያት ብቻ ነው። ከዚህም ቁጣ ለማምለጥ እውነተኛ ንሰሃ መግባት ነው። ትን ኢዩኤል 2፥13 "ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቍጣው የዘገየ፥ ምሕረቱም የበዛ፥ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ"። "በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት

አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም” (ዮሐ 3፥36)።

በአዲስ ኪዳንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስሜቱን በተለያዩ ቦታዎች ገልጿል። ለምሳሌ አለቀሰ ሉቃ 9:14፣ በማር 3:5 እና ማር 10፡14 ተቆጣ። በማርታና በማሪያም ወንድማቸው ጊዜ ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ (ዮሐ 11:35) ። የክርስቶስ ስሜቱ መቀያየር ከመለኮታዊ ሥራ እና ከሰዎች መዳን ጋር የተገናኘ ነበር።

## 2. የሰዎች ቁጣ፡-

መጽሐፍ ቅዱስን የማያውቁም የሚያውቁም ከጥቂት ሰዎች በስተቀር ከብሉይ ኪዳን ጀምረው የሚቆጡት እንደ እግዚአብሔር ዓይነት ቁጣ አይደለም። ማለትም ሰዎች የሚቁጡት ለራሳቸው ጥቅም፣ በትዕቢት፣ ሥልጣን ለማሳየት እና በጥቅሉ ለሥጋ ፍላጎታቸው ነው። ፈርኦን፣ሳኦል፣ ናቡከደነጾር፣ሀማ፣ሄሮድስ፣የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎችና ሌሎችም ሥጋዊ ቁጣ ተቆጥተዋል። ሥጋዊ እና የሰይጣን ቁጣ ቀጥሎ ችግር አምጪ እንጂ ለሰው ሌላ መፍቴሔ አያመጡም።

## 3. የሰዎች ግንኙነትና ቁጣ፡-

በሰዎች ህይወት የግንኙነቶች ብልሽት የመጀመሪያ ደረጃ የሚጀምረው በስሜት ላይ በሚፈጠረው ክስተት ነው። የስሜት መበላሸ በውስጡ ቁጣ ሊፈጥር ይችላል። የኤፌሶን 4:29-32 ኢንዲህ ይላል “እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያንጽና ሰሚዎችን የሚጠቅም ቃል እንጂ የማይረባ ቃል ከአፋችሁ አይውጣ። ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ”። እውነተኛ በሆነ ነገር ውስጣችን ሊቆጣ ይችላል። ነገር ግን የጽድቅ ቁጣም ቢሆን ለቅሬታ ለመራራነት ቦታ ማግኘት ስለሌለበት ብዙ ጊዜ ሳይወስድ ማስወገድ አለብን “ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት” (ኤፌ 4፡26 -27)።

## 4. የቁጣ ደረጃዎች፡-

ቁጣ እየጨመረ ከሄደ ንዴትን፣ ንዴት መራራነትን፣ መራራነት ጭቅጭቅ፣ ጭቅጭቅ ደግሞ ስድብን ከዚያ መለያየትን እና ቅሬታ ያመጣል “መራርነትን ሁሉ፣ ቍጣና ንዴትን፣ ጭቅጭቅና ስድብን ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ፣ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ” (ኤፌ 4፡31-32፣ቆላ 3:8)። ይህንን መሪህ ካልተከታተልን ቁጣ በጋብቻ፣ በልጆች እድገት እና በኑሮ ሁሉ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖና ብልሽት ያመጣል።

## 5. ምክር፡-

ቁጣን መቆጣጠር (Anger management) ማለት የአንተን ወይም የሌላን ሰው ቁጠኝነት ተገቢ በሆነ ወይም በአዎንታዊ መልኩ በማብረድ መፍትሔ የመስጠት ችሎታ ማለት ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ በተሞላ ንግግር ቁጣን ማስታገስ እንዳለብን ይነግረናል “የለዘበች መልስ ቍጣን ትመልሳለች፤ ሸካራ ቃል ግን ቍጣን ታስነሣለች” (ምሳ 15፥1) ። የጌታ ቃል ቁጣችን ፈንግሎ እንዲወጣ አይመክርም “ሰነፍ ሰው ቍጣውን ሁሉ ያወጣል፤ ጠቢብ ግን በውስጡ ያስቀረዋል” (ምሳ 29፥11)። ጥበበኛ፡ሰው ቁጣ መመለስ እንዳለባቸው ይመክራል “ፌዘኞች ከተማቸውን ያቃጥላሉ፤ ጠቢባን ግን ቍጣን ይመልሳሉ” (ምሳ 29፥8) ። ቁጣ የሥጋ ሥራ እንደሆነ ማወቅ (ገላ 5:19)። ቁጣ ቀጠይ ደረጃዎች እንዳሉት አውቀን መመለስ አለብን። ለቁጣ መቸኮል እንደሌለብንም በጥብቅ ይመከረናል “በነፍስህ ለቍጣ ችኩል አትሁን፥ ቍጣ በሰነፍ ብብት ያርፋልና” (ምሳ 7፥9 )። “ ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ” ቆላ 3፥8 ። በተጨማሪ መጽሐፈ ምሳሌን በትክክል ቢጠና ብዙ ይረዳናል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. እስካ አሁን ካላችሁ ጠቅላላ እውቀት በመነሳት ቁጣ ምንድ ነው?

2. ከላይ ያነበባችሁትን መሰረት በማድረግ ቁጣ ምንድ ነው?
3. ከላይ በተገለጸው ቁጣ እንዴት ሊመጣ እንደሚችል። ተወያዩ።
4. የእግዚአብሔር እና የሰው ቁጣ ልዩነቱ ምንድ ነው? አንድነቱስ?
5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማር 3:5፣ ማር 10:14 ለምን ተቆጣ?
6. ቁጣ በሰዎች ላይ ስለሚመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ተወያዩ
7. ኤፌ 4:31-32 በማንበብ ቁጣ በትክክል ካልተያዘ ወደ ምን ሊሸጋገር እንደሚችል ተወያዩ (ንዴትትና መራራነት ምንድ ናቸው? ቀጥለውስ ምን ሊያስከትሉ ይችላሉ?)
8. ፈቃደኞች ከሆናችሁ ተቆጥተን የምናውቅ ከሆነ ምን መጥፎ ውጤት እንዳመጣ ተወያዩ። ትክክለኛ ቁጣ ተቆጥቶ የሚያወቅ ሰው ካለ ይመስክር።
9. **ይህ ጥናት ቁጣን ስለመቆጣጠር የሰጠንን ምክር ተነጋገሩ**
10. ትክክለኛ ያልሆነ ባህርያችን እንዲቀየር ዛሬ እንጸልያን። ነገ ላለመድገም የሚያስታውሰንን ነገር ወይም ምልክት እናድርግ።

## *መደምደሚያ*

ቁጣን መቆጣጠር (Anger management ) ማለት የአንተን ወይም የሌላን ሰው ቁጠኝነት ተገቢ በሆነ ወይም በአዎንታዊ መልኩ በማብረድ መፍትሔ የመስጠት ችሎታ ማለት ነው ። መጠኑ ወይም ደረጃው ይለያይ እንጂ በሁላችንም ውስጥ ችግሩ አለ። ማንም ሰው አልቆጣም ቢል እርሱ ራሱን የማያውቅ ውሸታም ሊሆን ነው ማለት ነው።። ሁላችንም በየደረጃወ በመራርነት የመቆጣት ችግር አለብን፤ ሳናስበው ስንቆጣ ራሳችንን እናገኘዋለን። ስለዚህም በቤት፣ በሥራ ቦታ ፣ በመንገድ ላይ፣ በአምልኮ ስፍራዎች ወዘተ የችግሩ ሰለባዎች የምንሆንበት ብዙ ጊዜ አለ። ያ ደግሞ አደገኛን ነገር እንደ መሆኑ መጠን ውጤቱን በአስከፊ ሁኔታ በሕይወታችን የምንቀበልበት ጊዜ አለ። ቁጣ በጥበብ እንደጌታ ቃል ካልተያዘ አዕምሮን፣ልብን፣ጨጓራን እና ሌሎችንም የሰውነት ክፍሎችን ይጎዳል።

# ጥናት አራት

## ትህትና

**ዓላማ፡-**

የሥጋችንን ክብር ትተን በየትም ቦታ የድል ህይወት መኖር እንድንችል መመካከር እና መርዳት

**መግቢያ፡-**

በለፈው ጥናት ስለ ቁጣ ንዴትና መራራነት አጥንተናል። ከዚህ አሉታዊ የአማኝ ባህርይ እንዴት ራሳችንን መከላከል እንችላለን ለሚለው ጥያቄ አንዱ መፍትሔ በትህትና መኖር ስለሆነ በዚህ ጥናት የእውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትህትናን ትርጉም እና ጥቅሙን በማየት በራሳችን ህይወት መተግበር እንድንችል እንማራለን።

## የትህትና ትርጉምና መገለጫዎች

ትህትና በገላትያ 5:19-22 ከተጠቀሱት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ ነው። ትህትና ምንድ ነው? ለሚለው ጥያቄ ይህ ጥናት «ራስን ዝቅ ማድረግ፣ ከራስ ይልቅ ሌላ ሰው እንዲጠቀም መሻት፣ ከራስ ይልቅ ሌላ ሰው እንደሚሻል መቁጠር....” የሚለውን ትርጉም ይሰጣልና። ነገር ግን ይህ አባባል እንዳስብነውና እንደምንናገረው በተግባር ስንመጣ ቀላል ላይሆን ይችላል። በሥራ ለመተግበር ለወሰነ አማኝ ግን ለመንፈሳዊ ህይወቱ ጥቅሙ እጅግ የላቀ ነው። ትህትና ታዲያ በሰላምታ፣በንግግር/ድምጽ ዝቅና ከፍ በማድረግ፣ በውጫዊ አካል መገለጫ ብቻ ነውን?

የዚህ ጥናት አነሳስ የትዳር ጉዳይ አይደለም እንጂ አንድ ነገር መጥቀስ ይቻላል ራሱን ብቻ ወዳድ የሆነ ባል «አንቺ የእኔ፣የአንቺ የሆነው ሁሉ የእኔ፣ የእኔ የግሌ ግን የራሴ ብቻ ነው» ይላል ይባላል፡፡ ሚስትም እንደዚሁ ልትል ትችላለች። ታዲያ ከፍ ሲል የተመለከተውን የትህትና ትርጓሜ እንዲህ ላለ

ባል ወይም ሚስት ቢነግሯቸው ‹‹እናስ ምን ይተርፈኝና ነው ከሚስትህ/ከባልሽ ጋር ተጣብቀህ ኑር የምትሉኝ» ብሎ መጠየቁ ወይም መጠየቋ የማይጠረጠር መሆኑን የሥነ ጋብቻ ሊቃውንት፣ የሥነ ልቡና መማክርት ይመሰክራሉ፡፡ የጥቅም ትህትና የጽኑ ፍቅር ጠላት ነው። እንኳን ይኽን መሰል ራስ ወዳድ ባል ይቅርና «ሲያጣ ታግሶ ፣ ሲኖር ለግሶ»የተባለውም ማንም ባለትዳር ወይም ትዳር አልባ የሆነውም ሌላ ሰው ቢሆን ትህትናን፣ ማለትም «ታስቦ የሚደረግ ልባዊ የውስጥ ትህትናን» እንደ ገለባ የቀለለ አድርጎ ማሰቡ ሞኝነት ነው፡፡ ከልብ ካልታሰበ የልብ ትህትናን ለማሳየት፣ በተግባር ለመተርጎምም ቀላል አይሆንም፡፡

እኛ በዘልማድ ሰውን በከበሬታ ማነጋገር፣ በሥነ ሥርዓት ጉዳይን ለሰው መንገር፣ እጅ መንሳት፣ ሰውን በዛም አነሰ ከመቀመጫ ብድግ ብሎ ማሳለፍ፣ “ይምጡ” ብሎ ወደ መቀመጫ መምራትና የመሳሰለው ብቻ ‹‹ትህትና›› ሊመስለን ይችላል፡፡ ነገር ግን ላይሆንም ሊሆንም ይችላል፡፡ ያለንን ማካፈል በብዙ አገልግሎቶችም መሳተፍ እውነተኛ ትህትና ያለበትም የሌለበትም ሊሆን ይችላል። ትክክለኛው ‹‹ትህትና›› ማለት ሰው እንዲያው ጉዳይ እንዲፈጸምለት ወይም ያሰበው እንዲሳካለት የሚያሳየው ትህትና አይደለም። እርሱ‹ የአስመሳይነት ትህትና ብቻ ነው፡፡ ይህ ጥናት ውጫዊ ትህትናንም አይቃወምም። ነገር ግን ውስጣዊ እና ውጫዊ ትህትና አብረው መሄድ እንዳለባቸው ያምናል። እውነተኛ ትህትና ከልብ የመነጨ በውጪ የሚገለጥ ነው።

## ትህትና ለምን ያስፈልጋል?

1. ጌታ ትሁት ስለ ነበረና ክርስቶስን ለመከተል (ማቴ 11:29)
2. ጌታን የመፍራት አንዱ መገለጫ ስለሆነ ፡- “ 15፥33 “እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ትምህርት ነው ትሕትናም ክብረትን ትቀድማለች” ምሳ 15:33።

3. ራስን ከወድቀት ለመጠበቅ፡- “ሰው ሳይወድቅ በፊት ልቡ ከፍ ከፍ ይላል፥ ትሕትናም ክብረትን ትቀድማለች” ምሳ 18፥12።
4. ክብር ህይወት ስለሆነ፡- “ትሕትናና እግዚአብሔርን መፍራት ባለጠግነት ክብር ሕይወትም ነው” ምሳ 22፥4።
5. እግዚአብሔር ይመለከታል፡- “እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ” (ኢሳ 66፥2)።

## ምን እናድርግ?

ትህትናን በውስጣችን አስበንበትና አውቀን ካላደረገን ውጤታማ አንሆንም። ራሳችንን ማዕከል ያደረገ ህይወት የምንኖር ከሆነ በትህትና መኖር ካባድ ይሆናል። በትህትና ውጤታማ ለመሆን የሥጋን እና የዚህን ምድራዊ ክብር መርሳት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የውሸት ትህትና መኖር ሰላማችንን ሊያጠፋ ስለሚችል ካዛሬ ጀምሮ ማቆም ጥሩ ይሆናል። አብረን የምንኖር ወይም የምናገለግል ሰው የተሻለ እንደሆነ በተግባር ለማሳየት መጣር አለብን። ለማታየት የምናደርገው ትህትና ውድቀት አለው።

> “7 እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ፥ በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ።8 አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ። 9 እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥10 የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል።11 በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፥ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው፥ በሁሉም ነው።12 እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር

ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ።13 እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ። ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ።14 በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት" (ቆላ 3:7-14)።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከጠቅላላ እውቀት ወይንም ግንዛቤያችሁ መሰረት ትህትና ምንድ

   ነው?

2. ከላይ ያነበባችሁትን መሰረት በማድረግ ትህትና ምንድ ነው?

3. ውጫዊ እና ለራስ ጥቅም የሚደረግ ትህትና ምንድ ነው?

4. ውጫዊ ትህትና ከመንፈሳዊ ትህትና ልዩነቱ ምንድ ነው?

5. ምሳ 18፥12 እና 22:4 መሠረት ትህትና ለምን ያስፈልጋል?

6. ፊል 2:1-11 መሠረት
   ሀ. ጌታ ትህትናውን በተግባር ሲገልጠው ምን አደረገ?

   ለ. በጌታ ህይወት የትህትናው ውጤት ምን ምን እንደሆነ በዝርዝር ተነጋገሩ?

   ሐ. ከጌታ ህይወት ምን እንማራለን

7. ቆላ 3:7-14 በማንበብ፣ ትህትናን እንደ ልብሱ "ልበሱ" ማለት ምን ማለት ነው?

8. ለፍሬያማ አገልግሎትና ከሌሎች ጋር አብሮ ለመኖር (ለምሳሌ በትዳርና በአገልግሎት ቦታዎች) ትህትና ምን ዋጋ አለው? እንዴት?

9. ቁጣን፣ንዴትንና መራራነትን ከህይወታችን ከቤታችንና ከአገልግሎታችን ለማስወገድ ትህትና ምን ጥቅም አለው? ዛሬ በህይወታችን ጌታ ትህትናን እንዲያበዛ እንጸልይ። እንወስን።

**መደምደሚያ፡-**

የሥጋችን ሀሳብ ሁልጊዜ የትህትና ትርጉምና ተግባር ተቃዋሚ ነው። ምክንያቱም ሥጋችን የራስን ምድራዊ ክብር እና ጥቅም ፈላጊ ነው። ትህትና አስበንበትና አውቀን ማድረግ ያለብን ነገር ነው። ትህትና ክብር አለው። ፊል 2:1-11 እና ቆላ 3:7-14 በግላችን ማጥናቱን እንድንቀጥል እናበረታታለን።

## ጥናት አምስት

## ራስን መግዛት

**ዓላማ**

በእምነታችን ጉዞ ራሳችንን መግዛት ወይንም መቆጣጣር በሚያቅተን ነገር ላይ ድል እንድናገኝ መርዳት ነው፤

**መግቢያ፡-**

ራስን መግዛት በገላትያ 5:22 ከተጠቀሱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ መሆኑን ብዙዎቻችን እናውቃለን። ሁላችንም ባንሆን አንዳንድ ጊዜ ራሳንን መግዛት አቅቶን መሆን የማይገባንን ሆነን ራሳችንን እናገኘዋለን። ብዙ

ጥፋትም አድርሰን እናውቃለን። ራስን መግዛት እንደየሰው ዓላማ የተለያየ ቢሆንም በሁሉም የሥራ እና የኃይማኖት መስክ የተወደደ ነገር ነው። ራስን መግዛት ለዘለዓለም ህይወት ዝግጅት ላይም ብዙ አስተዋጽዖ አለው። ራስን መግዛት ከውስጣችን ሊውጣ የሚታገለንን ማንኛውንም የሥጋን ምኞት እና ፍላጎት በጌታ ጸጋ መቆጣጠር ማለት ነው። ለቁጣ ለቂም በቀልና ለጥላቻ ለሥጋዊ ጥቅም ለስካር ወዘተ በአምሮአችንና በልባችን ግፍት ከሚመጣ ፈተና ራስ ማደን እና ለሌሌችም ምስክር መሆን ነው። መድኃኒት ይመራል። ነገር ግን ጤንነትን ይሰጣል። አንዳንድ ጊዜ የጌታ ቃል ምክር እንደ መድኃኒት ነው። መንፈሳዊ ጤንነትንንና እድገታችንን ይጠብቃል። ራስን ስለ መግዛት መማርና ኖሮውን መለማማድ ወደ እምነት ብስለት ይመራናል።

## ራስን መግዛት በጌታ ቃል

ከላይ እንደተጠቀሰው በገላ 5:22 መሠረት ራስን መግዛት አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስም በመልዕክቱ በህይወታችን እንድንጨምር ከጠየቀን ነገሮች አንዱ ራስን መግዛት ነው (1ጴጥ 1:6)።

ራስን መግዛትን በስፓርተኛ የዕለት ኑሮ ምሳሌ ማየት ይቻላል "በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት፥ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ። የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ **ሰውነቱን ይገዛል፤** እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፥ እኛ ግን የማይጠፋውን። ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፥ ነፋስን እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም፤ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ **አስገዛዋለሁ**"( 1ቆሮ 9. 24፣ 27)። ይህ ሯጭ ወይም ስፖርተኛ ያገኘውን ሁሉ መብላትና ማድረግ አይችልም። ራሱን ይገዛል። ብዙ ሰዓት እንዲተኛ ለሥጋው ፈቃድ አይሰጥም። ራሱን መግዛት አለበት። ካልሆነ ከጨዋታውና ከሽልማቱ ውጪ ይሆናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ የሥጋ እና የዓለም ክብር ግብዣዎችን ራሱን በመግዛት እምቢ በማለት

የመጣበትን ዓላማ ፈጸመ። ራስን መግዛት በሀሳብ፣በቃላትና በተግባር የሚገለጥ ነገር ነው።ፈረስ ልጓም ከሌለው የሚሄድበትን አያውቅም።

## ራስን መግዛት ለምን ያስፈልጋል፤

1. ትክክል ላልሆኑ ነገሮች አይሆንም የሚል ምላሽ ለመስጠት።
2. ከክፉ የሥጋ ፈተናዎች ማለትም ከኃጢአት ከዓለማዊ ልማዶች ውድቀት ይከለክለናል፣ይጠብቀናልም። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የዮሴፍ ህይወት ነው።
3. ትዕግስት በህይወታችን እንዲዳብር ትልቅ አስተዋጾ አለው።
4. ጌታ የሰጠንን ወገኖች እንዳናጣቸው እጅግ ጠቃሚ ነው።
5. ራስን መግዝት ቁጣ፣ንዴትና መራራነት ፍሬ እንዳያፈሩ በር የሚዘጋ መንሳዊ መሣሪያ ነው።
6. ቤተሰብን፣ቤተ ክርስቲያንንና ሀገርን ለማስተዳደር ዋና መሳሪያ ነው።
7. በተጨማሪም ራስን መግዛት በአገልግሎትና በኢኮኖሚ የተዋጣልን ሰዎች እንድንሆን ትልቅ አስተዋጾ አለው

## <u>እንዴት ራሳችንን እንግዛ</u>

ሀ. ከመናገር እና ከማድረግ በፊት ደግሞ ደጋግሞ በማሰብ

ለ. ብናደርግ ሊመጣ የሚችለውን ወጤቱን በማሰብ

ሐ. ቃሉን በማሰላሰል እና ለጌታ እና ለቃሉ ታማኝ መሆናችንን በማሳየት

መ. ከዚህ በፊት ራሳችንን ባለመግዛት የደረሰብንን ችግሮችን ላለመድገም ማሰብ

ሠ. እራሳችንን ደግመን ደጋግመን ለጌታ መንፈስ አደራ በመስጠት

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከመግቢያ ሃሳብ መሰረት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማው ምንድ ነው?

2. ከላይ በተብራራው መሰረት ራስን መግዛት ማለት ምን ማለት ነው?

3. የጌታ ቃል ራስን መግዛትንን እንዴት ከመድኃኒት ጋር አነጻጸረው?

4. የራስን አለመግዛት አሉታዊ ተጽዕኖ ምንድ ነው?

5. 1ቆሮ 9. 24፣ 27 ራስን መግዛት ጋር ምን ይገናኛል? ተወያዩ

6. ራስን መግዛት ራሳችንን ከኃጢአት እና ትክክለኛ ካልሆኑ ዓለማዊ ፍላጎቶች እንድንጠብቅ እንዴት ይረዳናል? ምሳሌ በመስጠት ተወያዩ?

7. ራሳችንን አለመግዛት ከቁጣ፤ ከንዴት እና ከመራራነት ጋር ምን ግንኙነት አለው?

8. ከላይ ከተሰጡት ምክሮች እና የራሳችሁንም በመጨመር እንዴት ራሳችንን መግዛት እንችላለን?

9. ራስን የመግዛት መንፈስ ጌታ እንዲያበዛልን አንዳችን ለሌላችን በቅንነት እንጸልይ።

**መደምደሚያ**

ራስን መግዛት ራሳችንን፣ቤተ ሰብን፣ቤተ ክርስቲያንን እና ሀገርን እንደሚገባ ለመምራት እጅግ አስፈላጊ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው። ራስን መግዛት አላስፈላጊ ግጭቶችን እንዳንጋጭ ይከለክለናል። ራስን መግዛት በህይወታችን እንድንጨምር የጌታ ቃል ያስተምረናል።

# አገልግሎት

## የአገልግሎት እውቀት:- የት ላገልግል? ምን ላገልግል? እንዴት ላገልግል እና ለምን ላገልግል

## ለመልካም ሥራ (ኤፌ 2:10)

## ”መከሩስ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው “(ማቴ 9፡37-38)

### አጠቃላይ ዓላማ

ስለ አገልግሎት የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረንን ተመልክተን እያገለገልን ያለን በትጋት አገልግሎታችንን እንድንፈጽም በጌታ ቤት ምንም ዓይነት ተሳትፎ የለንም የምንል ደግሞ ወደ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንድንሰማራ ለማበረታታት

### አጠቃላይ መግቢያ

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እጅግ በጣም ብዙ ሥራ እና የአገልግሎት ክፍሎች ወይም ዘርፎች አሉ፣ የእግዚአብሔር ቃልም ሰው ከዳነ በኋላ በእግዚአብሔር ቤት ሥራ ፈት ወይንም ፍሬ ቢስ መሆን እንደሌለበት ያስተምራል። ሁሉም አማኝ ለመልካም ሥራ ተጠርቷል (ኤፌ 2:10)። ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያን ያለው እውነታ ግን **ጥቂት የተወሰኑ ሰዎች የተደራረበ አግልግሎት ተሸክመው ጥቂት የማይባሉት ግን ቤተ ክርስቲያን አምልከው ብቻ የሚሄዱ ናቸው**። እንደዚህ መሆኑ ደግሞ በሚያገለግሉት ሰዎች ኑሮ ላይ ጫና ከመፍጠሩም በላይ በአገልግሎቱ ጥራት እና ብቃት ላይም የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዖኖ መኖሩ ለሁላችንም ግልጽ መሆን ይኖርበታል። ስለዚህ ምንም እንኳን ስለ አገልግሎት ያለን አስተሳሰብና መረዳት አንዳችን ከሌላችን ሊለይ እንደሚችል የታወቀ ቢሆንም። የእግዚአብሔር ቃል ሁላችንም አገልጋዮች እንድንሆን የተጠራን መሆናችንን አበክሮ ስለሚያስተምር እያገለገልን ያለን አገልግሎታችንን በትጋት መፈጸማችንን መቀጠል ሲኖርብን እስካሁን ምንም አገልግሎት ውስጥ የሌለን እና ያልገባን ደግሞ አግልግሎት ለመጀመር ውሳኔ እና እርምጃ መውሰድ ይኖርብናል።

# አገልግሎት (ክፍል አንድ)

## ጥናት ስድስት

## አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፣ 1 ቆሮ 12፡5

**ዓላማ፡-**

መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ አገልግሎትን የሚሰጠውን ትክክለኛውን ፍቺ ወይንም ትርጉም በመዳሰስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙን ለማስጨበጥ የታሰበ ነው።

**መግቢያ፡-**

ስለ አገልግሎት ያለውን መረዳት እና አስተሳሰብ በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። አንዱ ገጽታ በተለምዶ መንፈሳዊ አገልግሎት ተብለው በሚመደቡት ስብከት፣ ትምህርት፣ ዝማሬ፣ አምልኮ፣ ምስክርነት፣ ጸሎት እና የመሳሰሉት ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፣ ሌላው ገጽታ ለቅዱሳን የሚደረግን አገልግሎት ወይንም ሌሎችን ለምሳሌ የተቸገሩትን ሰዎች ወይም እንግዶች በቤታችን መቀበል፣ የተቸገሩትን መርዳት፣ የተራቡትን ማብላት፣ የታረዙትን ማልበስ፣ ቤት ማጽዳት እና የመሳሰሉት ሲሆኑ። ሁሉም ሰው ባይሆንም ብዙዎች እነዚህን እንደ አገልግሎት አለመቁጠር ፡ አለያም አንዱን ከሌላው አሳንሶ ከመመልከት የተነሳ በአንዱ ላይ ትኩረት አድርጎ ሌላኛውን ቸል ብሎ የመመልከት አዝማሚያዎች በግልጽ ይታያሉ። ለዚህም መገለጫው አብዛኛው ሰው ለቅዱሳን ለሚሆን አገልግሎት የሚሰጠው ምላሽ በጣም የቀዘቀዘ እና አነስተኛ ሲሆን፣ ይሁን እንጂ በመድረክ እና በሚታዩ አገልግሎቶች በተመለከተ የሚሆነው የዚህ ተቃራኒውን ነው። ስለዚህ ለዚህ ዓይነቱ ችግር መፍትሄው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አገልግሎት የሚያስተምረው ፍቺ እና ትርጉም መመልከትና ሚዛናዊ የሆነ መረዳት መጨበጥ ያስፈልገናል።

ሁሉም ነገር ያለውን ጌታ እንዴት ማገልገል ይቻላል? ማገልገል የሚለው ቃል የወጣው አገልጋይ ወይም ባርያ ከሚለው ስም ነው። ተግባሩ ሁሉ የባርያ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። እንደየአውዱ የሚለያይ ቢሆንም ማገልገል ጌታን ማወደስ (ዘጸ 10:8፣ 10:11፣ 10,21)፣ፍጹም መገዛት እና አካሉን ማነጽ ወይም ሌሎችንንና እርስ በእርስ መተናነጽን ያጠቃልላል። ይህ

ሁሉ ለጌታ ክብር መሆን አለበት። አንደኛ ጴጥሮስ 4:9-11 እንደሚከተለው ያስነብበናል "9 ያለ ማንጐራጐር እርስ በርሳችሁ እንግድነትን ተቀባበሉ፤10 ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ **<u>እርስ በርሳችሁ አገልግሉ</u>**፤ 11 ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ **<u>የሚያገለግልም</u>** ቢሆን፥ **<u>እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤</u>** ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን"። መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕም እንዲህ ይለናል 35፥3 " ... አሁንም አምላካችሁን እግዚአብሔርንና ሕዝቡን እስራኤልን አገልግሉ"

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ዘጸ 10፡10-11 እና ቁ. 21፣ሐዋ ሥራ 17:25 እና ማር 10:45 በማንባብ አብራሩ። ጌታን እንዴት ማገልገል ይቻላል?
2. (አገልግሎት)፤ የሚለው የቃሉ ትርጉም ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ፍቺ ወይንም ትርጉም ምንድን ነው?
3. በመድረክ ከሚታይ ውጭ ሌላ አገልግሎት ይኖራል? መልሳችሁን አብራሩ ወይንም ምሳሌ ስጡ?
4. በሐዋ 6፡1-6 መሰረት ሐዋሪያቱ የገጠማቸው ችግር እና የተገኘው መፍትሄ ምን ነበር? የአገልግሎት ሁለትዮሽ ገጽታዎች ምንድናቸው?
5. 2ዜና: - 35፡3 ላይ ለሌዋውያኑ የተሰጠው ትእዛዝ ስለ አገልግሎት ምን ያስተምራል?
6. በ1 ቆሮ16፡15-16 መሰረት የአገልግሎት አንዱ ክፍል ወይንም ገጽታ ምንድን ነው?
7. 2ቆሮ 8፡1-5, ሐዋሪያው ጳውሎስ የመሰከረላቸው የመቄዶኒያ ቅዱሳን አገግሎታቸው ምን ነበር?

8. በሐዋ 1፡17 መሰረት አገልግሎት ወይንም ማገልገል ኃላፊነትን እና አደራን ከመወጣ ያለፈ ምን ትርጉም አለው?
9. ማቴ 25፡34-40ን በመመልከት ስለ አገልግሎት የተረዳችሁን አካፍሉ?
10. በሉቃ 8፡1-3 መሰረት የሚታየውን እና የማይታየውን አገልግሎት ለዩ? በሁለቱ መካከል ያለውን ትስስር አስረዱ?
11. እስከ አሁን ከቃሉ በተመለከትናቸው ሁለት የአገልግሎት ገጽታዎች መካከል መበላለጥ ወይንም ልዩነት አላቸው?
12. ከዛሬው የጥናት ክፍል ስለ አገልግሎት ፍቺ ወይንም ትርጉም ከዚህ ቀደም ካላችሁ መረዳት በተለየ መልኩ የተማርከውን አካፍል?
13. በዚህ እውነት እና መረዳት የልቦና እና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲሆን አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ።

## መደምደሚያ

ስለ አገልግሎት ሰፊ ትንታኔና ማብራሪያ ማቅረብ ይቻላል፤ ይሁን እንጂ ጠቅለል እና ሰብሰብ አድሮጎ ከዚህ እንደሚከተለው ልናየው እንችላለን፤ አግልግሎት ማለት ጌታ በሚሰጠን ጸጋ፣ በጊዜያችን፣ በጉልበታችን፣ በገንዘባችን፣ በእውቀት እና በችሎታችን ለሌሎች የምንሰጠው ግልጋሎት ወይንም ስራ ሲሆን ፣ ዓላማው ለእግዚአብሔር ክብር ለምንግስቱ መስፋት እና ለሰዎች ጥቅም ሊሆን ይገባል። አግልግሎት በመድረክ መስበክ፤ ማስተማር፤ በመዘምራን ቡድን ወይን በጸሎት ቡድን ማገልገል የአገልግሎት አንዱ ገጽታ ብቻ ሊሆን ይችላል። በጌታ ዘንድ ዋጋው የማይጠፋ አገልግሎት ለጌታ እንዳደረግነው ቆጥረን በቤተክርስቲያና እና ለሰዎች የምንሰጠው ግልጋሎት እና ስራ በጌታ ዘንድ መታሰቢያ አልለው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው አገልግሎትም ልዩ ልዩ እንደ ሆነ ሲሆን፣ በመካከላቸውም መበላለጥ ወይንም ልዩነት የለም

## ጥናት ሰባት (ክፍል ሁለት)

## የተሰጠንን ጸጋ ወይንም የአገልጎሎት ሽክምን መለየት እና ማሳደግ

“ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤” 1 ጴጥ 4፡10

**ዓላማ፡**

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የሰጠን የአገልግሎት ጸጋ ወይም ሽክምን ልብ ማለት እንድንችል ለማሳሰብ የተዘጋጀ

**መግቢያ፤**

በመጀመሪያው ጥናታችን ትክክለኛውን የአገልግሎት ትርጉም እንደ እግዚአብሔር ቃል ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ጌታ ኢየሱስ አደርገው ዘንድ የላከኝን ሁሉ ፈጽሜ አከበርኩህ በማለት ወደ አብ እንደ ጸለየው  እንዲሁ እኛ እንድናከናውነው እና እንድንፈጽመው የሚገባውን ሥራ እና አገልግሎት ሁሉ ፈጽመን አምላካችንን ማክበር እና ደስ ማሰኘት እንድንችል፤ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን እና አድርጉ የሚለንን ሁሉ ልናደርግ እና ልንፈጽመው እንድንችል{ የተሰጠንን የአገልግሎት ጸጋ ወይን ሽክም መለየት ይኖርብናል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ሰዎች ብዙ ጊዜ እንዲያገልግሉ ሲጠየቁ ላለማገልገል የሚሰጡት የተለመዱ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ዘጸ 4፡10
2. በ 1ጴጥ4፡10 ያለውን ሃስብ እንዴት ትረዱታላችሁ? የአገልግሎት ጸጋ ተቀብላችኋል የተባለው ለማን ነው?
3. ሮሜ 12፡4-6 የአካል ብልቶች ሥራን አና ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን እንዴት ነው በዚህ ክፍል ያነጻጸራቸው?

4. ማቴ25፡14-15 መሰረት ጌታው ለባሪያዎቹ ያካፋፈለው መክሊት ብዛት መስፈርቱ ምንድን ነበር?
5. ጸጋችንን እንዴት ለይተን እናውቃለ?
6. በውስጣችን ያለ ሸክም የሆነብን እና የሁለተናችንን ትኩረት ሊስብ የሚችል ነገር ሊኖር ይችላል ትላላችሁ? (ለምሳሌ ለታመመ ሰው መጸለይ)
7. እንድንፈጽመው በብርቱ የሚሰማን፣ ስናደርገው ደግሞ እርካታ የሚሰጠን ነገር ምንድን ነው ትላላችሁ? (ለምሳሌ የተቸገረን መርዳት)
8. የአገልግሎታችንን ጸጋ ማሳደግ የምንችልበት ትክክለኛው መንገድ ምንድን ነው ትላላችሁ?
9. ቤተክርስቲያን ሰው የምትፈልግበት ክፍተት እያለ እኔ ጸጋዬ አይደለም ወይንም አልተሰማኝም ማለቱ ትክክል ነው ወይ? መልሳችሁን አብራሩ፤
10. በሐዋ 6፡8 የእስጢፋኖስን ህይወት እና አገልግሎት በማየት ክፍተት ባለበት ቦታ እያገለገልን ጸጋችንን መለየት የሚቻል ይመስልሃል?
11. አንድ ሰው የሚያገለግልበትን ጸጋ በግልጽ ለይቶ እስኪያውቅ ድረስ ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ? ጌታ በፊቱ በሚያመጣቸው በሮች ሁሉ መሳተፍ አለበት እንላለን? አብራሩት
12. ከዛሬው ጥናት ለየእያንዳንዳችን ለአገልግሎት የተሰጠንን የእግዚአብሔር ጸጋ፣ እውቀት፣ ችሎታ፣ ጉልበት፣ጊዜ፣ ገንዘብ እና ሀብት እንዳለ አይተናል። ባለን እና በተሰጠን ነገር ሁሉ ለማገልግል እንጂ ስራ ፈት እና ፍሬ ቢስ እንዳንሆን አንዳችን ለሌላችን እንጸልይ።

**መደምደሚያ፣**

በቤተክርስቲያን ውስጥ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ያለ አንዳች አገልግሎት ቁጭ ብለው ጥቂቶች ግን በአገልግሎት ድርርቦሽ ሲደክሙ መመልከት ገሃድ የሆነ ጉዳይ ነው፣ ለዚህም ሰዎች የሚሰጡት ምክኒያት ይለያይ እንጂ ጠቅለል አርገን ስንመለከተው ለማገልገል አልተሰማኝም፣ ጸጋዬ አይደለም፣ አንዳንዴም አልተመቸኝም የሚሉት ምክኒያቶች ከብዙው ጥቂቶቹ ናቸው፡ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረን ሁላችንም ልናገለግልበት የምንችልበትን ጸጋ፣ እውቀት፣ ጉልበት፣ ችሎታ፣ ጊዜና ሀብትን ሰጥቶናል፣ ስለዚህ በተቀበልነውና ባለን ነገር ሁሉ ቤቱን እና ቅዱሳንን ለማገልገል መወሰን ይኖርብናል።

## <u>አገልግሎት፡-(ክፍል ሶስት)</u>

## <u>ጥናት ስምንት</u>

## <u>የአገልጋይነት ልብና መንፈስ፡- እንዴት እንገልግል</u>

“በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ፥ መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።” 1 ሳሙ 15፡22

**ዓላማ፣**

የእግዚአብሔር ቃል አገልግሎትን እንዴት ባለ ልብና መንፈስ ልንፈጽመው እንደሚገባ የሚያስተምረውን ለማስገንዘብ እና እንድንተገብር ለማበረታት

**መግቢያ፣**

አንዳንዶቻችን ትኩረታችን ከመጠን በላይ በአገልግሎቱ ላይ እናደርግና ከአገልግሎቱ ጋር ተያይዘው ሊታሰቡ የሚገባቸውን ቁልፍ ነገሮች እንዘነጋለን፣ በዋናነትም አገልግሎቱን የምንፈጽምበትን መንገድ እና አካሄድ እምብዛም አያስጨንቀንም፣ ከዚህም የተነሳ ከውስጠኛው ማንነታችን ጋር ያልተያያዘ ከህይወታችን ጋር ያልታረቀ አገልግሎት መሳይ ድርጊት ወይንም ስርዓት ስንፈጽም እራሳችንን እናገኛለን፣ አገልግሎትን በግዴለሽነት፣

በቻልታ፣ ወይንም በግብር ይውጣ መፈጸማችን የዚህ ችግር መገለጫዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። ይሁን እንጂ ትክረት ሊሰጥበት የሚገባው በትህትና እርስ በእርስ በመከባበር ለሌሎች ጥቅም እና ለጌታ ክብር መሆን ይገባዋል። በተሰጠን አገልግሎት ሁሉ በትጋት እና በፍቅር (1 ቆሮ 13:1-13) ማገልገል እጅግ ተገቢ ነው።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ማር 10፡45 መሰረት አገልጋይ ሊኖረው ስለ ሚገባው የአገልጋይነት ልብ የተረዳችሁትን አካፍሉ?
2. በዮሐ፡- 13፡12-14 መሰረት በምን ሁኔታ ነው እንድናገለገል ጌታ ምሳሌ የተወልን? አገልጋይ መሆንስ ምን ይጠይቃል?
3. ማር 10፡43-44 ጌታ በሚያምኑት መካከል እንዲሆን ያሳሰበው ትምህርቱ በተግባር ላይ ለማዋል የሚከብድ ይመስልሃል? መልሳችሁን በምሳሌ አስደግፉ፣
4. በፊልጵስዩስ 2፡3-4 መሰረት ስናገለግል ልብ ማለት የሚገቡን ሁለት ዋና ዋና ቁም ነገሮች ምንድን ናቸው?
5. ፊል 2፡4-9 ባለው ክፍል መሰረት ልናገለግልበት ስለሚገባን ሃሳብና መንፈስ የተረዳችሁትን አካፍሉ?
6. ሮሜ 12፡7-8 መሰረት ሐዋሪያው አማኞችን በመደጋገም የሚያሳስበው ነገር ምንድን ነው?
7. ሉቃ 12፡37 እና ማር 13፡34-7 አገልጋይ ወይንም ባሪያ ተግባሩን መፈጸም ያለበት እንዴት ባለ መንግድ ነው?
8. ማቴ25፡9-23 መሰረት የባሪይዎቹ ጌታ በተመለሰ ጊዜ ለምስጋና ያበቃቸው ዋና ነገር ምንድን ነው? ያተረፉት መክሊት ብቻ ነው?
9. 1 ሳሙ 15፡13-22 መሰረት እግዚአብሔር አገልግሎታችንን የሚመዝነው ከምን አንጻር ነው?

10. በዚህ ክፍል የሳኦልን <u>የታዘዝኩትን ፈጽሜለሁ</u> እና የሳሙኤልን <u>ለምን እግዚአብሔርን አልታዘክም</u>? አለመገባባት የተፈጠረው ከምን የተነሳ ነው?

11. ከዚህ ጥናት በኋላ አገልግሎትን በተመለከት ልንወስደው ወይንም ልናስተካከለ የሚገቡን እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

12. ከዛሬው ጥናት ስለ እውነተኛ የአገልጋይነት ልብ እና መንፈስ ለግልህ የቀረልህን አካፍል? ምናልባት ጎድለን የተገኘንበት ነገር ቢኖር ለንስሃ ጸሎት ጥቂት ደቂቃዎችን እንውሰድ (ጌታ ልባችንን ይመዝናል)

**መደምደሚያ፣**

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን እግዚአብሔር አገልግሎቱን መፈጸማችን ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱን የምንፈጽምበትን ልብ እና መንፈሳችንን ይፈልገዋል ወይንም ይመዝነዋል እንጂ (የትም ፍጪው ዱቄቱን ብቻ አምጪው እንደሚባለው አይደለም) ፣ ስለዚህ ማንኛውንም ዓይነት አገልግሎት ስንፈጽም እግዚአብሔርን እና ህዝቡን በሚወድድ ልብና እርሱን በሚፈራው መንፈስ ማገልገላችንን ወይንም መፈጸማችንን ልናስተውልና ልንጠብቀው ያስፈልገናል። ከዚህ ያነሰ የትኛውም ዓይነት ጥሩ እና ያማረ አገልግሎት የሚመስል ሁሉ ሰውን እንጂ እግዚአብሔርን ሊያስደንቀው ወይንም ሊያስገርመው አይችልም። ስለዚህ ይኸን በማወቅ አገልግሎታችን በእግዚአብሔር ፊት የሚጸናልን እንዲሆን እንጂ በእሳት ሲፈተን በእንጨት በሳር ወይንም በአገዳ እንዳነጸ ሰው ሥራችን የሚቃጠል እንዳይሆን ጌታ ማስተዋልና ጥበብን ይስጠን።

# አገልግሎት (ክፍል አራት)

## ጥናት ዘጠኝ

## የምናገለግለው ለምንድን ነው?

## ራዕይ 22:12፣ 1ቆሮ 15:58

**ዓላማ፤**

የምናገለግልበትን ምክንያት ከመጽሐፍ ቅዱስ ምን መሆን እንዳለበት ለማስገንዘብ

**መግቢያ**

ሁላችንም ለምን እንደምናገለግል ብንጠየቅ የምንለው ነገር ይኖረናል፡፡ ነገር ግን የሁላችንም መልስ አንድ ዓይነት ይሆናል ብሎ መገመት ግን የማይታሰብ ነው፡፡ የምናደርገውን ነገር ሁሉ የምናደርግበት ምክንያት የግድ ያስፈልገናል፤ አለበለዚያ ያለ ምክንያት የምናደርገውን ነገር ውጤትን ልንጠብቅበት አንችልም፡፡ እግዚአብሔርን እና ቅዱሳኑን ስናገለገል ግልጽ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት ያስፈልገናል፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር **ቃል ለምን እንደምናገለግል** የሚሰጠውን ምክንያቶች ምንድናቸው ብሎ በመመልከት የጋራ ግንዛቤን መጨበጥ እንችላለን፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የዮሐ፡- 21፡15-17, ጌታ የአገልግሎት አደራ በሰጠበት ሂደው በመደጋገም ያቀረበው ጥያቄ ምንድን ነበር?
2. ከዚሁ ክፍል ሳንወጣ ስናገለግል እርግጠኞች እንድንሆን የሚያስፈለገን ቁልፍ ነገር ምንድን ነው?
3. 2ዜና29፡11፣1ጴጥ2፡9 እግዚአብሔርን ከመውደዳችን ባለፈ እንድናገለግለው ሊቀሰቅሰን የሚገባው ምክንያት ምንድን ነው?
4. በኤፌ 2፡19-22, መሰረት በማገልገል እና በመገልገል ሂደት ውስጥ ግብ ወይንም ውጤቱ ምንድ ነው?

5. በኤፌ 4፡12-16 የክርስቶስ አካል እድገትም ሆነ መታነጽ እውን እንዲሆን የአገልግሎት ሚና ምንድ ነው ትላላችሁ?
6. በሮሜ 12፡4-8 የአንድን አማኝ የአገልግሎት ሚና አስፈላጊነትን በተመለከት ከክፍሉ የተረዳችሁትን አካፍሉ?
7. 2 ጢሞ 4፡7-8 ሐዋርያው ጳውሎስ ከምን ተነስቶ ነው የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ማለት የቻለው?
8. ራዕ2፡18-19 በትያጥሮን ለምተገኘው ቤተክርስቲያን ጌታ ማሳሰቢያ ምንድ ነበር? ከዚህስ ምን እንማራለን?
9. ማቴ 25፡19-23፣ ባለው ክፍል አገልግሎታቸውን በታማኝነት እየፈጸሙ የተገኙት ባሪያዎች ምን አጋጠማቸው? ራዕ22፡12 አነጻጽሩ
10. በዕብ 6፡10 መሰረት ስለ ማገልገል የተሰጠው ተስፋ ምንድ ነው?
11. በ1 ቆሮ 15፡58 ሐዋሪያው ለቆሮንቶስ አማኞች የሰጠቻው ምክር እና ማበረታቻ ሃሳም ምን የተረዳችሁን አካፍሉ፤
12. ከዛሬው ጥናት ለልባችሁ የቀረላችሁን ሃሳብ አካፍሉ፤

***መደምደሚያ፤***

ይኽን ጨምሮ ባለፉት ሶስት ተከታታይ የጥናት ክፍሎች **የት ላገልግል? ምን ላገልግል? እንዴት ላገልግል የሚሉት ሃሳቦች ተመልክተን በመጨረሻም ለምንድን ነው የምናገለግለው ለሚለውን ጥያቄ** የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን በዚህ ጥናት ተመልክተናል፤ ስናጠቃልለውም አግልግሎት ጌታ በሚሰጠን ጸጋ፣ በጊዜያችን፣ በጉልበታችን፣ በገንዘባችን፣ በእውቀት እና በችሎታችን ፣ ዓላማው ለእግዚአብሔር ክብር ለምንግስቱ መስፋት እና ለሰዎች ጥቅም ሊሆን እንደሚገባ አይተናል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ቃል የተረዳነውን እውነት ዘወትር እያሰብን የምናገልገል አገልግሎታችንን በታጋት እና በመሰጠት እንድንፈጽመው እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች እስከ አሁን ድረስ ሳናገለግል የቆየን ካለን ደግሞ አገልግሎት እንድንጀምር ጌታ ይርዳን፤

**ጥናት አሥር**

# ድኅረ ዘመናዊነት በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ!






የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ዳላስ ቴክሳስ

## ማውጫ

የድኅረ ዘመናዊነት (Postmoderninsm)

ማስታወሻ፡- ይህንን ጥናት ስናጠና በመጀመሪያ ቀን ክፍሉን በጋራ በማንበብ እንገነዘባለን። በሚቀጥለው ሳምንት ያነበብነውን በማሰላሰል የመወያያ ጥያቄዎችን እንሰራለን። መሪውም ቀድሞ በጥሩ ሁኔታ እንዲዘጋጅ አደራ እንላለን።ተባረኩ!

I. የጥናቱ አጠቃላይ መግቢያ

II. የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች

III. የድኅረ ዘመናዊነት ምንነትና ፍልስፍና

IV. ድህረ ዘመናዊነት የሚያመጣውና የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ

V. ድህረ ዘመናዊነትን ተቋቁሞ ድል የተሞላው የክርስትና ሕይወት ለመኖር

VI. መደምደሚያ

VII. ዋቤ መጽሐፍት


## I. የጥናቱ አጠቃላይ መግቢያ

***መሪ ቃል፡-*** *"ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና። ሌሊቱ አልፎአል፥ ቀኑም ቀርቦአል። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ። በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።"* (ሮሜ 13፡ 11-14)

አንድ ዘመን ሲያልፍ ሌላ ዘመን ይተካል። በእያንዳንዱ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች የየራሳቸው መልካምና መጥፎ የሚባል ገጽታ፣ ጠንካራና ደካማ ጎን፣ መልካም አጋጣሚዎችና ተግዳሮቶች፣ ችግሮችና ደህና ሁኔታዎች ሊፈራረቁ ይችላሉ። ሰዎች አንድን ዘመን ለማስታወስ ሲፈልጉ በወቅቱ የታወቁና መልካምም ሆነ መጥፎ ተጽዕኖ ያደረጉ ሰዎች ይጠቅሳሉ። ለምሳሌ ያክል በሙሴ፣ በኢያሱ፣ በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን ... በማለት እንደሚነገር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (**ነህ.12:7፣ 2ኛሳሙ. 3:1፤21:1፣ 1ኛሳሙ.4:25**)

የአዲስ ኪዳን የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የተተከሉበት ዘመን ነበር። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የታሪክ ዘገባ እንደሚያሥነብበን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ከመተከላቸው ጋር ተያይዞ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ስደት ውስጥ ያለፈችበት ዘመንም ነበር። ቤተ ክርስቲያን ስደቱን ተቋቁማ በጸናችበት ወቅት የስህተት ትምህርት ማዕበል በመምጣቱና የቅዱሳንን እምነት የማናጋት ተጽዕኖ በማስከተሉ ሐዋርያው ጳውሎስና ሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አማኞችን ከስህተት ትምህርት መጠበቅ ላይ አተኮሩ። ብዙ የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች የስህተት ትምህርትን ለመዋጋትና ቅዱሳን በእምነታቸው ተረጋግተውና በክርስቶስ ሥር ሰድደው እንዲኖሩ ለማነጽ የመጋቢነት ኃላፊነትን መወጣት ላይ አተኩረው መጻፋቸውን ከመልዕክቶቻቸው ይዘት መረዳት እንችላለን ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ቀጥሎ ሌሎች የተለያዩ ዘመኖች ወይም የታሪክ ክስተቶች እንደተፈራረቁና ቤተ ክርስቲያንም በዚህ ጉዞ ውስጥ እንደተፈተነች፣ በብዙ ተግዳሮት ውስጥ እንዳለፈችና ሥራዋን እንደሠራች ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ድርሳናት መረዳት ይቻላል። እንዲህ እያለ አሁን ካለንበት ዘመን ደረስን።

በዚህም በእኛ ዘመን የየተለያዩ መልካም አጋጣሚዎች፣ ተግዳሮቶችና በመልካምም ሆነ በመጥፎ ተጠቃሽ የሆኑ ሰዎች ታይተዋል። እኛም አሁን ያለንበትን ዘመን የመመርመርና ዘመናችንን ለመዋጀት የማሰብ፣ የማቀድ፣ ለጽድቅ በጽድቅ የመነሳትና የመትጋት ኃላፊነትና ግዴታ አለብን። የዛሬውን ኃላፊነታችንን ለመወጣትም በዚህ ክፍል የክርስቲያኖች፣ የቤተሰብና የቤተ ክርስቲያን ፈተና የሆነውንና ድኅረ ዘመናዊነት በመባል የሚጠራውን ፍልስፍና መዳሰስና መዘርዘር አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ ነው።

የዚህ ጥናት ዓላማም የድህረ ዘመናዊነትን ልዩ ልዩ ገጽታዎች በመቃኘት ለመንፈሳዊ ለውጥ በጋራ እንድንነሳ ማሳሰብና ማስተማር ላይ ያተኮረው ነው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ከጥናቱ አጠቃላይ ክፍል ምን ተረዳችሁ

2. የዚህ ጥናት ዓላማ ምንድ ነው?

## II. የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች

1. የድኅረ ዘመናዊነትን ምንነት ከሌሎች ዘመኖች ጋር በማወዳደር ለይቶ ለመረዳትና አሁን ያለንበትን ዘመን እንደሚገባ ማወቅ እንድንችል ለማስገንዘብ
2. አሁን ያለንበት የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና አስተምህሮን በመጽሐፍ ቅዱስ በመፈተሽ በእውነት ላይ መቆም እንድንችል ለማስገንዘብ
3. የድኅረ ዘመናዊነት ትምህርትና ፍልስፍና በሁለንተናዊ ማንነታችን፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ በመረዳት ራስን፣ ቤተሰብን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅ እንዲቻል ለማስገንዘብ ነው።
4. በድኅረ ዘመናዊነት ትምህርት፣ ፍልስፍናና ልምምድ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመቋቋምና ዘመኑን በመዋጀት የላቀ የክርስትና ሕይወት መኖር የሚቻልበትን መርህና ልምድ ለማካበት ታስቦ የተዘጋጀ ጥናት ነው።

## III. የድኅረ ዘመናዊነት ምንነትና ፍልስፍና

### 1. ምንነት

1) **ከቅደመ ዘመናዊነት**:- ድህረ ዘመናዊነት የሚለውን አሳብ ለመረዳት ከቃሉ ትርጉም መነሳትና ማብራራት አስፈላጊ ነው። **ድኅረ** ማለት **በኋላ** ማለት ሲሆን ይህም ከድኅረ ዘመናዊነት በፊት ሌላ ዘመን እንደነበረ አመላካችነት አለው። ይህ ከድህረ ዘመናዊነት በፊት የነበረው ዘመን ዘመናዊነት በመባል ይታወቃል። ዘመናዊነትም ይህን ስያሜውን ያገኘው ከዘመናዊነት ክስተት በፊት ከነበረው ዘመን ጋር ተነጻጽሮ ነው። ከዘመናዊነት በፊት የነበው ዘመን ደግሞ የቅደመ ዘመናዊነት ዘመን ነበር። ይህም ዘመን የቆየው **ከ500-1400 ዓ.ም** እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር ነው።

ይህ ዘመን በአብዛኛው የሚታወቀው እንደ ጥንትነቱ የቀድሞውን ታሪክ፣ ባህል፣ ሃይማኖትና ሥርዓት አክባሪ በመሆኑ ነው። ምንም ፍጹምና ሙሉ የሆነ ዘመን ባይሆንም ሥርዓትን በማክበር፣ ለአባታዊ ማኅበራዊ ስርዓቶች የሚገዛ፣ ብዙ ከባህል ወጎች ወይም ልማዶች (traditions) ጋር የተከለሰና የተበረዘ ስርዓት የነበረው ነው። በሃይማኖትና በባህል መካከልም ብዙ ልዩነት ባለመታየቱ በአብዛኛው የተረጋጋ ዘመን ነበር ለማለት ያስደፍራል።[1]

2) **ዘመናዊነት፡-** ከቅደመ ዘመናዊነት ቀጥሎ የተከሰተው ዘመን **ዘመናዊነት** በመባል ሲታወቅ ይህም ክስተት የታየው **ከ1400-1950** ዓ.ም እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር ባለው የጊዜ ክልል ነው። ይህ ዘመን ብዙ በርካታ ፈላስፎች የተነሱበት ዘመን ነበር። እነዚህ ፈላስፎች **የክርስትናን አስተምህሮ መሠረቱን ማፍረስ ትልቁ ሥራቸውና ትኩረታቸው ነበር።** ይህ ዘመን **"ዘመነ አብርሆት" (enlightment period)** በመባል ይታወቃል። የዚህ ዘመን ፍልስፍና መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ስልጣንን ማስወገድ አንዱ ትኩረቱ ነበር። የዚህም ምክንያቱ በሳይንሳዊ ምርምር ሂደት ውስጥ የማያልፍ ነገር ሁሉ ለእነርሱ "ቅዠት" ተደርጎ የሚቆጠር መሆኑ ነው። በእነርሱ አስተሳሰብ ይህን በማድረግ ማደግና መምጠቅ ሲችል ብቻ ነው ሰው እንደሚገባ ማሰብና ለችግሮቹ ሁሉ ትክክለኛ የሆነ መልስ ማግኘት የሚችለው። እነዚህ ሰዎች እንደሚያስቡት ሰው ከበላዩ የሚገዛውና የሚመራው ሥልጣንና ኃይል ካለ ከቶ ሰው ሊሆን አይችልም።[2]

3) **የድኅረ ዘመናዊነት**፡- ከዘመናዊነት ቀጥሎ የመጣው ዘመንና ለውጥ የድኅረ ዘመናዊነት አስተሳሰብ ነው። ከቅድመ ዘመናዊነትና ዘመናዊነት ዘመንና ልምምድ በኋላ የቀጠለው ድኅረ ዘመናዊነት በመባል የሚጠራው ዘመን ነው። ይህ ዘመን ከ1950 ዓ.ም ጀመሮ እስከ አሁን ድረስ ያለው እንደሆነ ቢነገርም ቃሉ ሥራ ላይ መዋል የጀመረው ከ1970 ዓ.ም በኋላ ነው። የድኅረ ዘመናዊነት ዘመን መሠረቱ ዘመነ አብርሆት ነው። እንደ አቶ ምኒልክ አስፋው ማብራሪያ "ድኅረ ዘመናዊነት በእጅጉ የሚታወቀው

[1] ምኒልክ አስፋው ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች ራዕይ አሳታሚ አዲስ አበባ 2004 ገጽ 170
[2] ምኒልክ አስፋው ገጽ 171

በአዲስነቱ ብቻ ሳይሆን ከሁሉ በላይ ግን አፍራሽነቱ ነው። ዛሬም በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች "*አይ ድሮ ቀረ*" ሲሉ ስለ ነገሩ አዲስነት ሳይሆን፣ ስለ ፈረሰውና ስለ ጠፋው ነገር እየተናገሩ ነው። የድኅረ ዘመናዊነት መሠረታዊ ባሕሪይም ይህ ነው- አፍራሽነትና ከላሽነት።"[3] ይህ በተለይም በምዕራቡ ዓለም በስፋት ተጽዕኖ ያመጣ እና ወደ ሌሎችም የዓለማት ክፍሎች የተዛመተና እየተዛመተ ያለ ባህል ነው።

## 2. የድህረ ዘመናዊነት ፍልስፍና

ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የሆነ ተግዳሮት የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና ነው። ይህ ፍልስፍና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለምም ሆነ በአገራችን በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ ነው። ዓለም እንደ አንድ መንደር መሆን በጀመረችበት በዚህ ወቅት የኢንተርኔትን መረብ በመጠቀም ማኅበራዊ ድረ ገጾች የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው። ድህረ ዘመናዊነት በብዙ አቅጣጫ በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ በመምጣቱ በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያን እየተጋፈጠችው ያለችው አብይ ተግዳሮት ሆኗል። ይህም የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና እግዚአብሔር የለሽነት አስተሳሰብና እምነት በመሆኑ ነው።[4]

የድኅረ ዘመናዊነትን አመለካከት የሚቀበሉና የሚያራምዱ ሰዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተበራከቱ መተዋል።[5] የድኅረ ዘመናዊነትን ፍልስፍና የሚያራምዱ የተለያዩ ሰዎች ለኅትመት በሚያበቋቸው ልብ ወለድ ጽሑፎችና ግጥሞች እንዲሁም በአንዳንድ ድረ ገጾችና የማኅበረሰብ ሚዲያዎች ላይ የሚቀርቡ ጽሑፎች ዋናው ግባቸው በእግዚአብሔር በሚያምኑ ሰዎች ላይ እምነትን የሚሸረሽርና የሚያፈርስ ተጽዕኖ መፍጠር ነው። ይህም የክርስትናን መሠረታዊ አስተምህሮ የሚገዳደር ሁኖ ይታያል።[6]

> *"ድኅረ ዘመናዊነት ንጽረተ ዓለም ሲሆን፣ ከዘመናዊነት ቀጥሎ የመጣና አሁን በበርካታ የምርምር እንዲሁም ሥነ ጽሑፎች ውስጥ የሚንጸባረቅ አመለካከት ነው። ይህ ንጽረተ ዓለም ዘርፈ ብዙ ቢሆንም*

---

[3] ምኒልክ አስፋው ገጽ 172
[4] ተካልኝ ዱጉማ ሕንጸት መጽሔት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እየተጋፈጠቻቸው የኑፋቄ አስተምህሮዎች Accssed 08/18/2015 http://www.hintset.org/2015/01/06/
[5] ተካልኝ ዱጉማ ሕንጸት መጽሔት
[6] ተካልኝ ዱጉማ ሕንጸት መጽሔት

*ዐይነተኛ መገለጫው ግን እውነት አንጻራዊ ናት፣ እውነት የግለ ሰቦችና የማኅረ ሰብ ፈጠራ ናት የሚል ነው። የድኅረ ዘመናዊነት ንጽረተ ዓለም ወደ ሃይማኖቶች ጎራ ሲመጣ ሁሉንም ሃይማኖቶች ትክክለኝነት የሚያውጅና ሃይማኖቶች የማኀበረ ሰብ ፈጠራዎች እንደ ሆነ የሚያቀነቅን ነው። ይህንን ንጽረተ ዓለም በመከተል አንዳንድ የሀገራችን ጸሓፍትም 'ሃይማኖቶች ሁሉ ልክ ናቸው' ወደ ሚል አልያም 'አምላክ የለም' ወደ ሚል ድምዳሜ መድረሳቸው የሚያመላክት ጽሑፎችን መጻፋቸውን መመልከት ጀምረናል። ይህም የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ተግዳሮት ሆኖ ይታያል።"* [7]

## የመጀመሪያው ሳምንት

## የመግቢያ ጥናት የመወያያ ጥያቄዎች

1. ስለ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?
2. መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ዘመናትን ለመግለጽና ለማስታወስ ሲፈልግ እንዴት ይገልጻል?
3. የቅድመ ዘመናዊነትን ምንነትና የትኛው ዘመን ክልል ቅደመ ዘመናዊነት ተብሎ እንደሚጠቀስ በዝርዝር ተወያዩ
4. የቅድመ ዘመናዊነትን ምንነትን የሚገልጹ እሴቶችና ክስተቶች ምን ምን እንደሆኑ በመግለጽ ተወያዩ
5. የዘመናዊነትን ምንነትና የትኛው ዘመን ክልል ዘመናዊነት ተብሎ እንደሚጠቀስ በዝርዝር ተወያዩ
6. የዘመናዊነትን ምንነትን የሚገልጹ እሴቶችና ክስተቶች ምን ምን እንደሆኑ በመግለጽ ተወያዩ
7. ስለ ዘመናዊነት ማወቅ ለእኛ ምን ይጠቅማል?

---

[7] ተካልኝ ዱጉማ ሕንጸት መጽሔት

## የመጀመሪያ ሳምንት ጥናት ማጠቃለያ፡- ሐዋ.13:36

መጽሐፍ ቅዱስ ስለተለያዩ ዘመናትና በዘመኑ ስለኖሩ ሰዎች ይገልጻል። በተለያየ ዘመን ስለኖሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ስለፈጠሩት መልካምና መጥፎ ገጽታ ለይቶ በመረዳት ከእነርሱ መማር መንፈሳዊነት ነው። የቅድመ ዘመናዊነትን ምንነትና ዘመን ክልል እንዲሁም የቅድመ ዘመናዊነትን መልካም እሴቶችና ክስተቶች በዘመናችን እንዲጸባረቁ የበኩላችን ጥርት እንድናደግርግ የሚሰጠው ጠቀሜታ ነው። የዘመናዊነትን ምንነት፣ የዘመን ክልልና እንዲሁም በዘመናዊነት የተፈጠሩ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎችና እሴቶች ለይቶ በመረዳት ካለፈው ዘመን መማር መቻል ብልህነት ነው። "**ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ፥" ሐዋ.13:36**

## የሁለተኛው ሳምንት ጥናት

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. **2ኛጴጥ.3:1-3 በማንበብ ዘመንን ማወቅ ለምን እንደሚጠቅም ተወያዩ**
2. የድህረ ዘመናዊ ጥሬ ቃል ትርጉምን በማብራራት ተወያዩ
3. የድኅረ ዘመናዊነትን ምንነትና የትኛው ዘመን ክልል ድኅረ ዘመናዊነት ተብሎ እንደሚጠቀስ በዝርዝር ተወያዩ
4. የድኅረ ዘመናዊነትን ምንነትን የሚገልጹ እሴቶችና ክስተቶች ምን ምን እንደሆኑ በመግለጽ ተወያዩ
5. ድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና መስፋፋትና ለእኛ ለአማኞች፣ ለቤተሰባችንና ለቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ተግዳሮት ነው ብለው ያምናሉ ከሆነስ እንዴት እንደሆነ በስፋት በማብራራት ተወያዩበት?
6. የድህረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና አስተሳሰባቸውን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ተወያዩበት።
7. ከዛሬው ጥናት ምን ተረዳችሁ

## የሁለተኛ ሳምንት ጥናት ማጠቃለያ፡-

የድኅረ ዘመናዊነትን ምንነትና ዘመን ክልል እንደሚገባ መረዳት አስፈላጊ ነው። ድኅረ ዘመናዊነትን የሚገልጹ የተለያዩ እሴቶችና ክስተቶች ምን ምን እንደሆኑ በመረዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ በመስጠት የግልና የሌሎችን እምነት መጠበቅ ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው። የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና እንዴት እየተስፋፋ እየመጣ እንደሆነ መንገዱንና ፍጥነቱን አጥብቆ መረዳት ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ እንድናደርግ ያግዛል። በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ እየመጣ ያለውን ይህን ፍልስፍና ለእኛ ለአማኞች፣ ለቤተሰባችንና ለቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ተግዳሮት በመሆኑ የድህረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና አስተሳሰባቸውን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ራስን በጽድቅና በቅድስና መጠበቅ ያስፈልገናል።

የሚቀጥለውን ጥናት ለሚቀጥለው ሳምንት አንብባችሁ እንዲትመጡ እናበረታታለን።

## IV. ድህረ ዘመናዊነት የሚያመጣውና የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ

### 1. ሰዎች ለክርስትና ያላቸውን መሠረታዊ አቋም ማናጋት

የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና ቋሚ መታወቂያ "ቋሚ እና አምላካዊ እውነት" የለም የሚል ነው። እውነት አንጻራዊ ነው የሚለው አቋማቸው ሰዎች ነገሮችን ሁሉ ከእውነት መኖር አንጻር ሳይሆን ከአንጻራዊነት አንጻር መመልከት እንዲጀምሩ ተጽዕኖ ያሳድራል። ማለትም እውነት እንደየሰው አረዳድ እንጅ አንድ ወጥ የሆነ እውነት እንዳለ አያምኑም። የድህረ ዘመናዊነት አስተሳሰብ መስመር የአንድ ነገር ልክ፣ መስፈርት፣ መርህና መሠረት ሊኖር ስለማይችል ሁሉም ሰው የራሱ አንጻራዊ የሆነ እውነት እንዲኖረው ያበረታታል። የሚፈጥረው ተጽዕኖም ሰዎች ራሳቸውን፣ ሌሎችን ሰዎችና ነገሮችን መመዘን እንዲሁም ትክክል እንደሆኑና እንዳልሆኑ ማወቅ እንዳይቻል ያደርጋል።

በድህረ ዘመናዊነት ውስጥ አንድ ቋሚ እውነት አለመኖሩና ሁሉ ነገር አንጻራዊ ተደርጎ መወሰዱ ምዕመናን የክርስትና እምነት መሠረታቸው ላይ ለዘብተኛ እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል። የክርስትና ሕይወት መርህ

የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ከቃሉ የበላይነት አንጻር ሳይሆን ከአንባቢውና ከተርጓሚው አንጻር ብቻ የሚታይ እንዲሆን ስለሚያስተምር ቃሉን ሊያቃልል ይችላል። ንጉሥ ዳዊት ስለእግዚአብሔር ቃል እውነትነት ሲገልጽ እንዲህ ይላል:- "*ጽድቅህ የዘላለም ጽድቅ ነው፥ ቃልህም እውነት ነው።... የቃልህ መጀመሪያ እውነት ነው፥ የጽድቅህም ፍርድ ሁሉ ለዘላለም ነው።*" **(መዝ 119፥ 142 እና 160)** ሐዋርያው ዮሐንስም አሳቡን በማጠናከር እንዲህ ይላል:-"*በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው*" **(ዮሐ 17፥ 17)** የድህረ ዘመናዊነት ፍልስፍና ግን ይህንን መርህ ሞኝነት አድርጎ የሚቆጥር ሲሆን እንደዚህ ያለውን እውነት የሚቀበሉ ሰዎችን አቋምም በእነርሱ ብቻ የሚደገፍ አንጻራዊ ወይም የእነርሱ ብቻ የሆነ እውነትን የሚያንጸባርቅ እንደሆነ ይቆጥራል።

በተጨማሪም የክርስትና ዋስትናና መሠረት የሆነውን ኢየሱስን መንገድ፣ ሕይወትና እውነት እንደሆነ የማይቀበልና የሚቀበሉትንም ለማስካድና የኢየሱስን የክርስትናን ማዕከላዊነት ለማንኳሰስ የሚተጋና የመስቀሉን ሥራ ዋጋ የሚያሳጣ ፍልስፍና ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን ሲናገር እንዲህ ይላል:-"*ቶማስም:- ጌታ ሆይ፥ ወደምትሄድበት አናውቅም፤ እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው። ኢየሱስም:-* ***እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።*** " **(ዮሐ 14፥ 5-6)**[8] *አለው።* እውነት ጌታችን ኢየሱስ ብቻ ነው!!

## 2. ሰዎች በሕይወታቸው ተጠያቂነትን እንዳይለማመዱ ማድረግ

ድህረ ዘመናዊነት ሰዎች በበላይ ስልጣንና ኃይል ሥር መኖር የለም ብለው እንዲያምኑና ሕይወታቸውን ለስልጣን ለማስገዛት ፈቃደኛ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ተጽዕኖ በማሳደር ተጠያቂነት የሌለበት ግለኝነትንና ራስ ገዝነትን መርህ ያደረገ ሕይወት እንዲኖራቸው የሚያበረታታ ፍልስፍና ነው። ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል በሚናገረው መሠረት ሁሉን ለሚችልና

[8] ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ፈተናዎች ኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 2009 ዓ.ም ገጽ 293-299

ሁሉን ለፈጠረ አምላክና ህያው ባለስልጣን ለሆነው ለእግዚአብሔር ቃል ራሳቸውን እንዳያስገዙና እንዳይታዘዙ ይልቁንም እንቢተኛነትን እንዲያዳብሩም ያበረታታል።

እግዚአብሔር ትዳርና ቤተሰብን ሲሰጥ በቤተሰብ ውስጥ ራሱን የቻለ የስልጣንና የኃላፊነት ተዋረድ አለ። በትዳር ውስጥ ባል በፍቅር በሆነ እና አምባገነናዊ የበላይነትን በማያንጸባርቅ አስተዳደር ሚስትን የሚመራ አፍቃሪ እንዲሁም አገልጋይ መሪ ሊሆን ይገባል። ሚስትም በፍቅር ለባሏ የመገዛትና የመታዘዝ ኃላፊነት እንዳለባት መዘንጋት የለበትም። እነዚህ መርሆዎች ከተዘነጉ ትዳር በግጭት፣ በመለያየትና በፍች እንዲደመደም ሊደርጉ ይችላሉ።

በባለትዳሮች መካከል ብቻ ሳይሆን በወላጅ እና በልጆች መካከል ያለው የወላጅና የልጅ ግንኙነትም በፍቅር፣ በመከባበር፣ በመታዘዝ ላይ የተገነባ እንዲሆን ቃሉ ያዘናል። የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና ግን ልጆች ከወላጆች ጋር ትክክለኛና ጤነኛ ግንኙነት እንዳይኖራቸው ከፍተኛ ተጽእኖ ይፈጥራል። በአሉታዊ ተጽእኖው ስር ልጆች ከወደቁም ወላጆቻቸውን የመስማት፣ የመታዘዝና የማክበር ልማድን ሊያጠፉባቸውና ግለኝነትና ራስ ገዝነትን አጥብቀው እንዲፈልጉና እንዲለማመዱ ሊጋብዛቸው ይችላል። ልጆች በቤተሰብ ውስጥ ለወላጆቻቸው መታዘዝን ከጣሉ በትልቁ ቤተሰብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ለአገልጋዮች ብሎም ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ባለው ማኅበራዊና መንግሥታዊ ግንኙነት ለስልጣናትና ለበላይ አካላት የመታዘዝና የመገዛት ልማድ ይጠፋባቸዋል። ወደ ራስ ገዝነት ባሕል ልምምድ ውስጥም ተዘፍቀው ይገባሉ።[9]

## 3. ሰዎች በሕይወታቸው በዓላማና በግብ እንዳይኖር ማድረግ

እንደ ማንኛውም በእግዚአብሔር መልክና አምሳል እንደተፈጠረ ሰው በእያንዳንዳችን ላይ እግዚአብሔር ዓላማ አለው። ከዚያም ባሻገር በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ዳግም እንደተወለደ መንፈሳዊ ሰው እግዚአብሔር በእኛ ላይ የተለየ ዓላማ እንዳለው ቃሉ አጥብቆ ይነግረናል። "*እኛ ፍጥረቱ ነንና፤*

[9] ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ <u>የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ፈተናዎች</u> ገጽ 293-299

*እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።"* (**ኤፌ 2: 10**) ይህ ሁኖ እያለ የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና ግን ወጣቱ ትውልድ በሕይወቱ ዓላማና ግብ እንዳይኖረውና ራሱን እያገነነ እንዲሁ በዘፈቀደና በአጋጣሚ እንዲኖር የሚያበረታታ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የቀድሞ የሕይወቱን እምነት፣ ልምምድና እሴት እያነሳ አሁን በክርስቶስ ያገኘውንና የሚጠብቀውን ዓላማና ግብ እያሳየ በዚህ መርህ መኖርን ዋና የሕይወቱ ጉዳይ አድርጎ አቅርቧል። ከዚህ መርህ ማፈግፈግንም እንደ ጉዳት ይቆጥራል። ቢሆንለት በሞቱ ክርስቶስን በመምሰል በኋላው ያለውን እየረሳ ወደ ፊት ለመያዝ በፍጥነት በመዘርጋትና ዛሬን በደረሰበት እየተመላለሰ ይኖር ነበር። ይህ ዓይነቱ ዘመን አይሽሬ መርህ ከድህረ ዘመናዊነት መርህ ጋር በግልጥ ተጣራሽ ነው።

*ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ **ጉዳት** ቈጥሬዋለሁ። አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ **ጉዳት** እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ **ጉድፍ** እቈጥራለሁ፤ እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ **እንድመስለው እመኛለሁ**። አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ **እፈጥናለሁ**። ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት **እቈጥራለሁ**፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ **እዘረጋለሁ፥** በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን **እፈጥናለሁ።**እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ፤ በአንዳች ነገርም ልዩ አሳብ ቢኖራችሁ፥ እግዚአብሔር ይህን ደግሞ ይገልጥላችኋል፤ ሆኖም በደረስንበት በዚያ እንመላለስ።* (**ፊል 2: 7-16**)

የክርስቲያን የሕይወት ግብና ተስፋ በዚህ ምድር የሚቆምና የሚጠናቀቅ ሳይሆን በላይ በሰማይ የሚቀጥል ሰማያዊና ዘላለማዊ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን በዚህ ምድር ብቻ ተስፋ የምናደርገው ከሆነ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ምንም የሌለን ምስኪኖች እንደሆንን ቃሉ እንዲህ ሲል ይመሰክራል:-"*በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።*" **(1ኛቆሮ 15: 19)**[10]

## ሦስተኛ ሳምንት ጥናት

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና ትምህርት በመዘርዘር ተወያዩበት
2. የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ አስተምህሮ በመፈተሽ በስፋት ተነጋገሩበት
3. የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና ትምህርት በአማኞች ሕይወት ውስጥ ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ አንዱ ለክርስትና ያላቸውን መሠረታዊ አቋም ማናጋት ሲሆን በምንና እንዴት እንደሆነ በስፋት ተወያዩበት

   1) አምላክ 2. እውነት 3. የቃሉ የበላይነት

4. የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና ትምህርት በአማኞች ሕይወት ውስጥ ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ አንዱ በሕይወታቸው ተጠያቂነትን እንዳይለማመዱ ማድረግ ሲሆን በምንና እንዴት እንደሆነ በስፋት ተወያዩበት

   1) በግል ሕይወት
   2) በትዳር
   3) በቤተሰብ ወይም በወላጆችና በልጆች
   4) በቤተ ክርስቲያን

[10] ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ፈተናዎች ኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 2009 ዓ.ም ገጽ 293-299

5. የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና ትምህርት በአማኞች ሕይወት ውስጥ ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ አንዱ በሕይወታቸው በዓላማና በግብ እንዳይኖር ማድረግ ሲሆን በምንና እንዴት እንደሆነ በስፋት ተወያዩበት

6. ከዛሬው ጥናት የገባችሁን ነገር በአጭሩ አካፍሉ።

## የሦስተኛ ሳምንት ጥናት ማጠቃለያ ፡- ኤፌ.5:15-33፣ 6:1-9

የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር በከፍተኛ ሁኔታ የሚቃረን መሆኑ ግልጽ ነው። የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና ትምህርት በአማኞች ሕይወት ውስጥ ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ መካከል ለክርስትና ያላቸውን መሠረታዊ አቋም በማናጋት ነው። ስለ አምላካችን ፣ ስለእውነት፣ ስለኢየሱስ ክርስቶስና የቃሉ የበላይነት በመጽሐፍ ቅዱሳችን በማረጋገጥ ትምህርታቸውን ከንቱ ልናደርግ ይገባል። የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍናና ትምህርት በግል ሕይወታችን፣ በትዳር፣ በቤተሰብና በቤተ ክርስቲያን መካከል አንዱ ለሌላው ተጠያቂና ስልጣን ተግዥነትን በማጥፋት ሰው ሁሉ በራሱ መንገድ እንዲጓዝ የሚያበረታታ በመሆኑ አጥብቀን በአቅልና በኑሮ ልናወግዘው ይገባል።

## IV. ድህረ ዘመናዊነትን ተቋቁሞ ድል የተሞላው የክርስትና ሕይወት ለመኖር

ክርስቲያን የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲጠበቅ ለማድረግና ከክህደቱ ለማስመለጥ እንዲቻል ወጣቱ ከሌሎች ወጣቶች፣ ከወላጅና ከቤተሰብ፣ ከቤተ ክርስቲያንና ከአገልጋዮቿ እንዲሁም ከሚመለከታቸው መንፈሳዊ ድርጅቶችና ከሌሎች አካላት ጋር በጋራ በትብብር አብሮ መሥራት ተገቢ ነው። የተሻለ ትውልድ ለማሥነሳት መንቀሳቀስ የሚቻለው በዚህ ሂደት ብቻ ነው። ይህንን ጥረት በተሳካ መልኩ በማከናወን ድህረ ዘመናዊነትን ተቋቁሞ በድል ለመኖር የሚከተሉትን ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው፡-

## 1. መረዳት:- ድኅረ ዘመናዊነት የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ መረዳት

መፍትሔ ለማምጣት መወሰድ ያለበት የመጀመሪያውና ቀዳሚው እርምጃ ወጣቱ ትውልድም ሆነ ሌሎች አካላት ድኅረ ዘመናዊነት በአማኞች በተለይም በወጣቱ ትውልድ ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚገባ መረዳት ነው። ይህም እርምጃ የድኅረ ዘመናዊነትን ፍልስፍና መሠረታዊ ትምህርት፣ ዓላማና ግብ፣ እሴት እና ልምምድ ምንድን እንደሆነ ለመረዳት ጥረት ከማድረግ ይጀምራል። የድኅረ ዘመናዊነት ፍልስፍና በወጣቱ የክርስትና ሕይወት፣ አስተሳሰብ፣ እሴት፣ ዓላማ፣ ግብና ኑሮ ላይ እያመጣውና እየፈጠረው ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ መረዳት መቻል አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም ሆነ ሌሎች ሐዋርያት እስከ ዛሬ እኛ የምንጠቀምባቸው መልዕክቶች የተጻፉት በግምት አልነበረም። እያንዳንዳቸው ስለሚጽፉበት ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት ጥረት የሚያደርጉት ስለችግሩ ምንነት እና በአማኞች የክርስትና ትምህርት፣ ሕይወት፣ በቃሉና በቤተ ክርስቲያን ላይ ስለሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ በመረዳት ነበር። የሐዋርያው ጳውሎስን ልምድ እንደምሳሌ አድርገን ብንወስድ ነገሮችን ለመረዳት ከቀሎዔ ቤተሰቦች መረጃ መስማቱን ማስታወስ በቂ ነው *"ወንድሞቼ ሆይ፥ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና።"* **(1ኛቆሮ 1: 11)** እንደገናም ራሳቸው የቆሮንጦስ አማኖች እንደ ጻፉለት በማስታወቅ *"ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር፥ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው።"* **(1ኛቆሮ 7: 1)** የሚል ምላሽ ሰጥቷል።

ድኅረ ዘመናዊነት በአማኞች ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመረዳት ሌሎችን ሰዎች መጠየቅ፣ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጽሑፎችና መጻሕፍትን በማንበብ፣ ማኅበራዊ ድረ ገጾችን በመጎብኘት፣ እውቀቱ ያላቸውን ሰዎች ጋብዞ በመማርና የፓናል ውይይት በማድረግ መረጃ ማግኘት። ከዚያም የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰድ።

## 2. መመገብ፡- በእግዚአብሔር ቃል እውነትና የበላይነት ሥር እንዲሰዱ ማድረግ

የእግዚአብሔር ቃል በሁሉም ነገር ላይ የበላይ፣ ህያው ሁኖ የሚሠራና የሰውን ሁለንተናዊ ማንነት መለወጥ የሚችል አቅም ያለው መሆኑን በማስረዳት ማስተማር የድህረ ዘመናዊነትን አፍራሽ ተጽዕኖ መቀነስ ወይም መግታት ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ ነው። ለሰው ልጆች ከፍተኛ ችግርና ጥያቄ መልስ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ እንደሆነ ወጣቱ ትውልድ ይበልጥ እንዲያውቅ መረዳት ያስፈልጋል። ስለእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ምን ይላል? የሚለውን ጥያቄ በማንሳትም ስለ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ያለው እውነት ለወጣቶች ማስጨበጥ ተገቢ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው፡ *"የአምላኬ መንገድ ፍጹም ነው፥ የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው፥ በእርሱ ለሚታመኑት ሁሉ ጋሻ ነው ።"* **(መዝ 18: 30)** ፣ ሕያውና የሚሠራ ደግሞም ሁለንተናን የሚመረምርና የሚለውጥ*"የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤"* **(ዕብ 4: 12)** ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወጣት ለሆነው፣ ለመንፈሳዊ ልጁና የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ለሆነ ለጢሞቴዎስ እንዲህ እያለ ይመክረዋል:-*"ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፥ እያሳቱና እየሳቱ፥ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ። **አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥** ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤ ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።"* **(2ኛጢሞ 3: 13-17)**

በዚህ ክፍል የምንማረው መርህ ቢኖር በወቅቱ በነበሩት ክፉና አታላይ ሰዎች በኩል ለተፈጠረው የስህተት ትምህርት በመጀመሪያ ከአሁን በፊት በተማረው ጸንቶ እንዲኖር፣ ምን፣ ከማንና መቼ እንደተማረ ጠንቅቆ እንዲያስታውስ፣ የእግዚአብሔር ቃል ምን ያክል ጠቃሚ እንደሆነ በማረጋገጥ በቃሉ እንዲጸና፣ ለመልካም ሥራ እንዲዘጋጅበት፣ ሌሎችን የማያሳፍር የቃሉ አገልጋይ በመሆን እንዲመግብ በማሳሰብ ይመክረዋል።

ምዕመናን ለቃሉ የምትሰጡት ሥፍራ ሊታሰብበት ይገባል። **ለቃሉ ቅድሚያ መስጠት**፣ ቃሉን የበላይ ማድረግና በየጊዜው ቃሉን ለመማርና ለመታዘዝ የልብ ዝግጅትና ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። በግላችንም **የጥሞና ጊዜን በማጠናከር ራስን ማሳደግ** ይገባል። ጢሞቴዎስ ለሕይወቱና ለአገልግሎቱ የጠቀመው ከቤተሰቡ ያገኘው ክርስቲያናዊ ትምህርት፣ ምክርና ምሳሌነት ነው። በጽድቅ ሕይወት በመመላለስ እንዲኖሩ በማበረታታት ክርስትና ኋላ ቀርነትና ብዙ ከዓለም እንደጎደለባቸው እንዳያስቡ ቃሉን እንደሚገባ መመገብ ይጠይቃል። አማኞችም በመንፈሳዊ ሕይወት መሠረት የሚጣለውና እውነተኛ ማንነት የሚገነባበትና የምንለማመድበት ተቋም ቤተሰብ ነው። ስለዚህ በቤተሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጸሎት ኅብረት ተጠቃሚ መሆንና ቃሉን ለመስማት እንዲሁም ለመማር የተዘጋጀ ልቦና ሊኖር ይገባል።

ዘመን ሳይለውጠው ዘመን ተሻጋሪ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አትዘንጋ !!

ቤተ ክርስቲያን ለምዕመኖቿ ለእግዚአብሔር ቃል ከፍተኛ ሥፍራና ትኩረት እንዲሰጡ ፍላጎት መፍጠርና መመገብ ይገባታል። ወጣቶች መሠረታዊ የክርስትና እምነታቸውን እንዲረዱ፣ በየዕለቱ በሕይወት በሚገጥማቸው ፈተና በድል መወጣት እንዲችሉ፣ ዐመጽን እየጠሉ ጽድቅን የሚያስወድድ የቃሉ ጉልበት እንዲያገኙና ሥር በመስደድ የማይናወጡ እንዲሆኑ መመገብ ያስፈልጋል:; ወጣቶችም ለቤተ ክርስቲያን በመታዘዝና በቤተ ክርስቲያን ባሉ አገልጋዮች ቃሉን ለመማርና ለመጠቀም ትህትና የተሞላው ልብ፣ ትጋትና ትብብር ማድረግ ተገቢ ነው። "*ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና*

*ገሥጽ ምከርም። ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ።"* **(2ኛጢሞ 4: 2-4)**[11]

### 3. መርዳት:- ለበላይ ስልጣን መታዘዝና መገዛትን እንዲለማመዱ መርዳት

ቤተሰብ፣ ቤተ ክርስቲያንና ወጣቱ ትውልድ በጋራ በመተባበር በአማኞች በተለይም በወጣቶች ሕይወት፣ ምርጫና ውሳኔ ላይ የእግዚአብሔርን ቃል የበላይ እንደሆነና እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲወስኑና ለፈቃዱ እንዲታዘዙ መርዳት ያስፈልጋል። የምዕመናን አንዱ ፈተና ምርጫና ውድድር በበዛበት በዚህ ዘመን በሰከነ ሁኔታ ከክፉ መልካሙን፣ ከዐመጽ ይልቅ ጽድቅንና ከጊዜያዊው ይልቅ ዘላለማዊውን ለመምረጥ እንዲችሉ የቃሉን የበላይነት አምነው እንዲቀበሉና እንዲታዘዙ መርዳት ያስፈልጋል።

ለእግዚአብሔር ቃል ባለስልጣንነት መታዘዝን የሚለማመዱ አማኞች በቤተሰብ መካከል የወላጅነትና የልጅነት መከባበርና መታዘዝ ባለበት ተቋም ውስጥ ለመኖር ላይቸገሩ ይችላሉ። ልጆች ወላጆችን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማክበርና መታዘዝን እንዲማሩና እንዲለማመዱ መርዳት ተገቢ ነው። ልጆች ለቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደንብና መመሪያ ራስን ማስገዛት መንፈሳዊነት እንጂ ኋላቀርነት እንዳልሆነ ሊገነዘቡ ይገባል።

> *ግለሰቦች ለቤተሰብ እና ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደንብና መመሪያ ራስን ማስገዛት መንፈሳዊነት እንጂ ኋላቀርነት እንዳልሆነ ሊገነዘቡ ይገባል!*

ትክክለኛ በሆኑ ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተሰብና ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለመንግሥት አካላትና ባለስልጣን መታዘዝና መገዛት እንደሚገባም ቃሉ ይነግረናል።

---

[11] ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ፈተናዎች ገጽ 293-299

*"ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምሥጋና ይሆንልሃል፤ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። ስለዚህ ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው። ስለዚህ ደግሞ ትገብራላችሁና፤ በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና። ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፥ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፥ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፥ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።"* **(ሮሜ 13፡ 1-7)**

*"ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና። ሌሊቱ አልፎአል፥ ቀኑም ቀርቦአል። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ። በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።"* **(ሮሜ 13፡ 11-14)**[12]

## የአራተኛ ሳምንት ጥናት የውይይት ጥያቄዎች

1. ከባለፈው የተማራችሁትን የድኅረ ዘመናዊነት አሉታዊ ተጽዕኖ ማለትም በግል መሠረታዊ እምነታችን፣ በእርስ በርስ ሊኖረን ስለሚገባ ተጠያቂነት እንዲሁም በክርስትና ሕይወታችን ሊኖረን ስለሚገባ ዓላማ በመጥቀስ ተወያዩበት

---

[12] ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ፈተናዎች ገጽ 293-299

2. ድህረ ዘመናዊነትን ተቋቁሞ ድል የተሞላው የክርስትና ሕይወት ለመኖር
    1) የእያንዳንዱ አማኝ ኋላፊነት
    2) የባለትዳሮችና የቤተሰብ
    3) የቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና አገልጋዮች በመጥቀስ በስፋት ተወያዩበት
3. ድህረ ዘመናዊነትን ተቋቁሞ ድል የተሞላው የክርስትና ሕይወት ለመኖር የመጀመሪያው እርምጃ ምንድን ነው ይላሉ?
4. ድህረ ዘመናዊነትን ተቋቁሞ ድል የተሞላው የክርስትና ሕይወት ለመኖር ሁለተኛው እርምጃ ምንድን ነው ይላሉ?
5. ድህረ ዘመናዊነትን ተቋቁሞ ድል የተሞላው የክርስትና ሕይወት ለመኖር ሦስተኛ እርምጃ ምንድን ነው ይላሉ?
6. በዚህ ምዕራፍ ልትጠነቀቁበት እና እርምጃ ልትወስዱት የሚገባ አዲስ የተማራችሁትን አሳብና ልምምድ እርስ በርስ ተከፋፈሉ።

## የአራተኛ ሳምንት ጥናት ማጣቃለያ፡- 2ኛጢሞ.3:1-17

ድህረ ዘመናዊነትን ተቋቁሞ ድል የተሞላው የክርስትና ሕይወት መኖር ምርጫ ሳይሆን ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ድረስ የዘመኑን ተግዳሮት ለይቶ መረዳትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን በማስተማር ምዕመናን በእምነታቸው ሥር በመስደድ መጽናት እንዲችሉ አጥብቆ ቃሉን መመገብ የቤተ ክርስቲያን ኋላፊነት ነው። ዘመን ተሻጋሪ በመሆኑ የቃሉ እውነት የተለያዩ የዘመኑን አስተሳሰቦችና እምነቶች መመዘን፣ የቃሉን የበላይነት ማረጋገጥና እንደ ቃሉ በትዳር፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያንና በአገር ደረጃ መታዘዝን፣ መገዛትንና ተጠያቂነትን መልመድና ማስለመድ መቻል ይኖርብናል።

## ዋቤ መጽሐፍት


1. ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ፈተናዎች ኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 2009 ዓ.ም
2. ምኒልክ አስፋው ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች ራዕይ አሳታሚ አዲስ አበባ 2004 ዓ.ም
3. ተካልኝ ዱጉማ ሕንጻት መጽሔት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እየተጋፈጠቻቸው ያሉት የኑፋቄ አስተምህሮዎች Accssed 08/18/2015http:// www.hintset.org/2015 / 01/ 06/

# ጥናት አሥራ አምስት

## ፀሎትና እምነት

ለጥናቱ የንባብ ክፍሎች ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይሆናል

**ዓላማ ፡-**

ፀሎትና እምነት የተያያዙ ወይም አንድ ላይ የሚሄዱ መንፈሳዊ መርሆች መሆናቸውን ለመዳሰስ

**መግቢያ ፡-**

ፀሎት የእግዚአብሔር ሀሳብ መለኮታዊ ድንጋጌ ነው። ፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምናደርገው ጥልቅ ንግግር ሲሆን የማያቋርጥና የሚቀጥል ነው። ፀሎት ሃይማኖታዊ ሆኖ ኃይል የሌለው ሳይሆን በትክክለኛ መስመር ውስጥ ገብተን ከጸለየን ውጤት የሚያመጣ የእግዚአብሔር መንግሥት ሚስጢራዊ የጦር መሳሪያ ነው (ዮሐ፡17፡20-21) ። ብዙ አማኞች ጸሎትን ከእምነት አንዳንድ ጊዜ ሳያውቁት አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በቸልተኝነት ይለያያሉ። እምነትን ከጸሎት መለየት ኃይል ማጣትን ያስከትላል።

በዚህ ጥናት ጸሎት ከእምነት ጋር እንዴት እንደሚያያዝ በተለያዩ መንገዶች እናያለን

## 1. ጸሎት በክርስቶስ ህይወት፡-

በምድር በኖረበት ጊዜ የጌታ ኢየሱስ የሕይወት ሚስጢር ከአባቱ ጋር በጸሎት የነበረው የየቀኑ የሕይወት ዘይቤ ነው። 5000 ሰዎችን ከመገበ በኋላ እና በባሕር ላይ የተነሳውን ነፋስ ጸጥ ከማሰኘቱ በፊት ወደ ጸሎት እንደሄደ ማር 6:45-46 ይነግረናል። በተጨማሪም ማር 1:23፣ ማር 14:35-39፣ማቴ 9:28 እና ሌሎችንም ክፍሎች ማየት ይቻላል። … ደቀ መዛሙርቱ ጌታን

እንዲያስተምራቸው ከጠየቁት ነገሮች አንዱ ጸሎት ነው (ሉቃስ፡11፡1)። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደሚያስረዳን ጌታ ካረገ በኋላ ሐዋርያትም ብዙ ጸልየዋል (ሐዋ ሥራ ምዕራፍ 1,2,4,5,10,12 ... )።

## 2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት-

እምነት በእግዚአብሔር ቃል የተነገረ ነገር ግን ገና ሳንጨብጠው የምናምነው ነገር ነው። **"እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው" (ዕብ 11:1)** ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሚገኙ እውነታዎች ላይ የተመሰረተ ነው። እምነት ከእግዚአብሔር ቃል እውቀት ይጀምራል። ያለ ቃሉ እውነተኛ እምነት ሊኖረን አይችልም። ከላይ የተመለከትነው የዕብራውያን መልዕክትም ይህንኑ ያብራራል። እግዚአብሔር ተስፋ የሚደረግ ነገር ግን ገና ያልጨበጥነውን ነገር ተናግሮን አምነነው አሜን ብለን ስንቀበል **እምነት** ይባላል። እምነት ግን በነሲብ (በጨፈና) አንድን ነገር አምናለሁ ማለት አይደለም።

## 3. ጸሎት ከጌታ ጋር ህብረት ማድረግ ነው፡-

ከሰዎች ጋር በደንብ እንተዋወቃለን የምንለው አብረናቸው ጊዜ በማሳለፋች እና በመጨዋወት ነው። ባህሪያችንን የምንተዋወቀው ይሄንን፤ ያንን፤ ይወዳሉ፤ አይወዱም የምንለው ጊዜ ወሰደን አብረን በመሆን ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በዚህ መልኩ የሚታይ ነው። ለእግዚአብሔር ጊዜ ሰጥተን አብረን በማሳለፍ ፤ ማንነቱ (ባህሪውን) የበለጠ የምናውቀው በዚህ ፀሎት በሚባለው የእግዚአብሔር ሚስጢራዊ መሳሪያ ነው። እግዚአብሔር ፀሎታችንን የሚሰማን ልክ ስለሆንን ሳይሆን ልጆቹ ስለሆነን ነው። ልጆችን የምናዳምጣቸው ልክ ስለሆኑ አይደለም። ልጆች ስለሆኑ ነው (ገላ 4:6፣1ዮሐ 2:1-3) ። ጌታ ልመናችንን የሚያዳምጠን በእርሱ ማስተዋል ጥልቀት እንጂ ጸሎታችን ልክ ስለሆነም አይደለም።

4. **<u>እምነት በንግግርና በስሜት በተግባር በመገለጥ ይታያል፡-</u>**

ፀሎት የእግዚአብሔርን ሕያው የሆነውን ቃል የምንናገርበት በአፋችን ቃሉን በእምነት የምናወጣበት ነው። በእምነት ፀሎት ቃሉን ወደ እግዚአብሔር እናቀርባለን። እግዚአብሔር አባትም ቃሉን ያመለክታል ፤ እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ደግሞ እምነት ነው። (ዕብራ.11፡6) ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም። ጌታም ይፈጽማል (ኤር.1፡12) "እግዚአብሔርም እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ" ይላል። በእምነት ጨርቁን ነካች (ማር፡5፡25-34) (ፀሎቷ የእምነት ነበር) ጨርቁን ብነካ እድናለሁ !! የእግዚአብሔር ቃል በፀሎት ጊዜ ዋናው መገኛችን ነው። ((ኢሳ.55፡11፣ ዕብ.4፡16 ፣ኤር፡33፡3) ።

በሉቃስ.11፡1 ደቀ መዛሙርቱ እንዲያስተምራቸው የጠየቁት ብዙዎችን አብልቶ ማጥገብ ፤ ማዕበልን ፀጥ ማድረግ፣ አጋንንትን ማስወጣት፣ በሽተኞቹን መፈወስ፣ የሞተን ማስነሳትና በውሃ ላይ መራመድ ሳይሆን ፀሎትን ነው። ደቀ መዛሙርት ጌታ በተግባር ሲያደርግ ካዩት ነገሮች አንዱ መጸለይን ነበር (ማር፡-1፡35)። ማርቲን ሉተር "ብዙ ስራ ባለኝ ቀን ብዙ እፀልያለሁ ብዙ ሥራ የሚሰራው ከስራው ይልቅ በፀሎት ነው" ይል እንደ ነበር ይነገራል።

5. **<u>ምን እናድርግ?</u>**

ፀሎት የምንለማመደው ነገር ነው:: ስለ ፀሎት ተምሮ ልምምድ አለማድረግ አይጠቅምም ። ስላወቅነው ብቻ ሕይወት አይሆንም ፤ ፀሎትን በአዕምሮ እያደነቁ አለመለማመዱ በቴሌቪዥን የሰውነት የማጎልመስ ዘዴ (exercise) ሲያደርጉ እያየን ሳናደርገው ብናደንቅ ብቻ ለኛ ጥቅም

እንደማይሰጥ ሁሉ ፀሎትንም የየቀኑ ልምምድ ካልሆነ ምንም ጥቅም አይኖረውም።

ከእግዚአብሔር ጋር በፀሎት ብዙ ጊዜ ስናሳልፍ ምን ማድረግ እንደሚገባን ይነግረናል። የሕይወታችንን መመሪያ ይሰጠናል።

6. **ማወቅና ማድረግ የምገባን መርሆች፡-**

- የሕይወታችንን መመሪያ ከእግዚአብሔር የምንቀበለው በቃሉ መሠረት በፀሎት ነው።
- (ሉቃ.18፡1) ሳንታክት እንድንፀልይ ይነግረናል።
- በሌላ በምንም ነገር ልንደርሳቸው የማንችላቸውን ሰዎች በፀጋው ዙፋን በኩል በፀሎት ልንደርሳቸው እንችላለን (ዕብ.4፡16) ።
- ፀሎት በእምነት ወደ እርሱ እንድንጮህ ያመላክተናል። (ኤር.33፡ 3)
- ንስሀ የምንገባው በፀሎት ነው፤ የምንማልደው የምናመሰግነው ፤ ነገሮችን የምናስለውጠው በፀሎት ነው። በፀሎት ውስጥ አምልኮ አለ። (1ጢሞ.2፡1-2)
- ፀሎት የኛ ኃላፊነት ነው።
- ፀሎት የማንኛውም ክርስትያን (የክርስቶስ ተከታይ) መሠረቱ ሊሆን የሚገባው ነው።
- ፀሎት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሲፀለይ እምነትን እና ፀሎትን ያያይዝልናል። ፀሎት እና እምነት አንድ ላይ የሚሰሩ ነገሮች ናቸው። እምነት ፀሎትን እንዲሰራ የሚያደርግ መንፈሳዊ ልምምድ ነው። ስለዚህ ሁለቱም አብረው የሚሄዱ መንፈሳዊ እውነቶች

ናቸው። የሁለቱ አብሮ መሆን መንፈስ ቅዱስን ማዕከላዊ ያደርገዋል (ኤፌ. 6፡18) (ምሳሌ 15፡8) (ሮሜ 8፡26)

- ማንኛውም የፀሎት ችግር ከቃሉ እውቀት ማነስና ካለማመን የሚመጣ ችግር ነው (ማቴ፡4፡4) ሰይጣን ጌታን በበረሃ ሲፈትነው የጌታ መልሱ ከሕይወት ቃል እያወጣ ነበር ።
- በመናገራችን ብዛት ሳይሆን የምንሰማው በእምነታችን ነው (ማቴ6፡7) ።
- (1ነገስት ምዕ፡18፡25-29) የምንፀልየው ለሚሰማ፣ ለሚመልስ፣ ለሚዳስስ ፣ለሚናገር እናለሚለውጥ አምላክ ነው። ሰዎች እንጨት ጠርበው አምነው ይፀልያሉ። እኛማ ለሚሰማ : ሰማይና ምድርን ለፈጠረ ኤልሻዳይ ለተባለው የሁሉ ፈጣሪ ሁሉን ቻይ ለሆነው ፀልየን እንዴት አንሰማ ክብር ለእርሱ ይሁን!!
- የእግዚአብሔርን ቃል ደጋግመን በምንፀልይበት ጊዜ የታሰረ ይፈታል: የእግዚአብሔር ዓይን በፃድቃኖች ላይ ስለሆነ (ያዕ፡5፡ 16):: ጆሮዎቹ ለጻድቁ የተከፈተ ስለሆነ ስንፀልይ ይሰማናል።
- “የፃድቅ ሰው ፀሎት ብዙ ውጤት የሚያስገኝ ታላቅ ኃይል አለው።” ለኃጥያተኛው ደህንነት ያስገኛል፤ በጨለማው ስራ የታሰሩትን ያስፈታል፤ ለበሽተኛው ጤንነት ያስገኛል። (ሮሜ፡1017) …. (ኤፌ.6፡17)::
- የምስራቹን ቃል ስንሰማ እምነት በውስጣችን ይፈጠራል። የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መንፈስ ቅዱስ እንደመሪያችን አድርገን መያዝ አለብን። (ፀሎታችን በመንፈስ ቅዱስ የተመራ መሆን አለበት)

- እምነት የተሰጠን ተአምራቶችን እንድናደርግ አይደለም እግዚአብሔርን እንድናስደስት እንጂ፤ ይህም ከሁሉ የሚልቅ ተአምራት ነው። ዲያቢሎስም ተአምራት ማድረግ ይችላል። እግዚአብሄርን ግን ማስደሰት አይችልም። (ዕብ፡11፡6) ቅዱሱን እግዚአብሔርን ማስደሰት በራሱ ለኛ ክብር ነው። (ሰውን ማስደሰት እንኳ እንዴት ከባድ ነው።) (ዕብ.11፡6-40) እናም አንዳንዴ እግዚአብሔር የሌለ የሚመስልበት ጊዜአት ሊኖር ግድ ነው። ይህ እምነት አንዳንዶችን እንዲያመልጡ ያስችላቸዋል። ያው እምነት ሌሎችን ደግሞ እዚያው በትዕግስት እንዲፀኑ ያደርጋቸዋል።
- ከማምለጥ ይልቅ ታግሶ መቆየት የሚበልጥ እምነትን እንደሚጠይቅ እና እግዚአብሔር የሌለ በሚመስልበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዳለ ማመን እግዚአብሔርን የሚያስደስተው እምነት አይነት ነው።ሐይላቸው እርሱን በመፈለግ እርሱን ያከበሩትን ዘንድ ልባቸውን ያዘጋጁ ሁሉ ያለ ዋጋ አይቀሩም። (ማርቆ.10፡29-30) (1ቆሮ፡1፡30) (ያዕ፡2፡18)
- አንድ ሰው እምነት አለኝ የሚል ከሆነ የሚታይ ማስረጃ ከሌለና ምንም ፤ ምንም መልካም ስራ ከሕይወቱ የማይወጣ ከሆነ አለኝ ያለው ነገር ውሸት ነው ይላል። ያዕቆብ ስራ የሌለው እምነት የሞተ ነው። ምንም ሊያከናውን አይችልም። (ያዕ፡2፡22) እምነት ራሱን በስራ ይገልጣል። (ዕብ፡11) ላይ የቅዱሳኑን ታሪክ ስንመለከት እምነታቸውን የገለፀውን ስለ ስራቸው በማውራት ነው። ከእግዚአብሔር ባህሪ አንደኛው እምነት ነው። እግዚአብሔር ብርሃንን ሳያይ ይሁን አለው። ሁሉንም ሲፈጥር ይሁን ብሎ ጠርቶ ነው።

**ተጨማር ትኩረት፡- አመንኩ ስለዚህ ተናገርኩ**

እምነት ሁሌ ትክክለኛ አቅጣጫ ያሳየናል።
የደህንነታችን እጅ እምነታችን ነው። (ማቴ፡16፡1-20)
የጌታ ኢየሱስን ትልቁን የሕይወቱን ቦታ የያዘው ፀሎት ነው።
ሉቃስ፡10-19 ሊከናወን የሚችለው በእምነት ፀሎት ነው።
ፀሎት የአባትና የልጅ ቋንቋ ነው፤ የመኖርም ምልክት ነው።
ደስታችሁ ፍፁም እንዲሆን ፀልዩ ይላል። <u>ለካ መፀለይ ነው ደስታችንን ሙሉ የሚያደርገው</u> ። **ራሱ ጸሎቱ ሳይሆን በጸሎት ከጌታ ጋር መገናኘቱ ዋና ነገር ሊሆን ይገባል።** በሰማይ ፈቃድህ እንደሆነ እንዲሁም በምድር ትሁን። በጌታ ቃል ተመዝኖ ካላለፈ በምድር ላይ የሚካሄደው ነገር ሁሉ የወደቀው ሰው ፈቃድ ነው። የወደቁ አጋንንቶች ፈቃድ ነው። የጌታ ፈቃድ “ለምኑ ይሰጣችኋል: ፈልጉ ታገኛላችሁ: አንኳኩ ይከፈታል” ዛሬም እንለምናለን: ዛሬም እንፈልጋለን: ዛሬም እናንኳኳለን። መለመን ለማይችሉ ተሰፋ ቆርጠው መፈለግ ላቃታቸው ብርታት ሃይል አጥተው ማንኳኳት ላቃታቸው እንለምናለን ፤ እንፈልጋለን ፤ እናንኳኳለን።

**የመወያያ ጥያቄ**

1. ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም። “ ዕብ.11፡5፡6) እምነት እንዴት እግዚአብሔርን ሊያስደስተው ቻለ? እምነት ራሱ ምንድነው? (እስኪ ጊዜ ወስዳችሁ ከቃሉ አንፃር እንዲሁም ከራሳችሁ ልምምድ ጋር እያዛመዳችሁ ተወያዩበት)

2. ፀሎትና እምነት እንዴት ይያያዛሉ? (ሀሳቡን ሰፋ አድርጋችሁ ከራሳችሁ ልምምድ ጋር ምስክርነትም ካላችሁ ያንን በማካፈል ተወያዩበት (መሰረታችን ስለሆነ በአንክሮ ተወያዩበት)
3. ፀሎት ምንድነው? ሃሳቡን በተለያየ መልኩ ተወያዩበት (የፀሎትን ትርጉም ከሰጣችሁ በኋላ ምን ምን ዓይነት ፀሎቶች እንዳሉ ተወያዩ)
4. ለምኑ፤ ፈልጉ፤ አንኳኩ የሚሉትን ቃላቶች እያንዳዳቸውን በምሳሌ ተወያዩ (በውስጣችሁ እንደ ስዕል እስኪቀረጽ ድረስ)
5. በቃሉ መሰረት መፀለይ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ነው የሚፀለየው?
6. የየግል የፀሎት ሕይወታችሁን (ድካምም፤ አለማመንም ካለበት በግልፅነት) ተወያዩ!

ይሄንን አይነት ውይይት ሊያነቃቃን ሊያስተካክለን በድካምም ሆነ አንዳንዴም እምነት አልባ መሆናችን ሌላ ሰውም ጋ መኖሩን እና በነገሩ ብቸኞች አለመሆናችንን ያሳያል) በውይይታችሁ ከተጽናናችሁ ከተበረታታችሁ በኋላ በእምነት ፀሎት ፀልዩ።

7. ከክርስቶስና ከሐዋርያት የጸሎት ህይወት ምን እናማራለን?
8. (ያዕ.2፡18-22) በዚህ ምንባብ መሰረት ስራ የሌለው እምነት የሞተ ነው; ሲል ምን ማለቱ ነው። በስራ ነው የሚፀድቀው እንደሚሉት አይነት ነው?
9. ይህንን ጥያቄ ተወያይታችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ በአንድነት በመስማማት በእምነት ጸልዩ (የጸሎት ርዕስ ያለው የጸሎት ርዕሱን ያቅርብ ከሌለም ለእርስ በርሳችሁ በእምነት በርህራሔ ፀልዩ (ለሰዎች ስንፀልይ የራሳችንም እንቆቅልሽ ይፈታል ።) ተባረኩ!!!

**መደምደሚያ፡-**

መዳናችን በእምነት ነው ። ጌታን ያስደነቀው እምነት ነው። ሌላው አለማመን ነው። እኛን ከሌሎች የለየን እምነት ነው። ሰው ሁሉ እምነት አለው። ነገር ግን እምነታችን በምን ላይ ነው የተደገፈው? እምነታችን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መሆን አለበት። ሌሎች የሚያምኑት ነገር አለ ስንል በተለያየ ነገር ሊያምኑ ይችላሉ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ያልተመረኮዘ ነው። በእምነትና በመጽናት የእግዚአብሔር ቃል በኛ ላይ ይሰራል። እምነት መቀበያ ነው እንጂ መጠበቂያ አይደለም። ፀሎታችንን በእምነት አቅርበን በእምነት እንቀበላለን።

**ፀሎት፡-** አምላክ ሆይ!! ይሄንን ጥናት ላጠኑ ሁሉ በእምነት በጌታ በኢየሱስ ስም ደጆች ይከፈቱ ሞገስህን በእነርሱ ላይ አድርግ፤ ፀሎታቸው በእምነት የተሞላ በመንፈስ ቅዱስ የተመራ ይሁን ፀጋህን አብዛላቸው ።

ሁሌ እንደስምህ እንደቃልህ ስለሆንክልን ክብር ምስጋና አምልኮ ላናተ ይሁን ። ክብሩን ጠቅለህ አንተ ውሰድ። በጌታ በኢየሱስ ስም ሁሉን በሚገዛው አሜን !!!!

# ጥናት አሥራ ስድስት

## ነቢያትና የትንቢት ስጦታ

**ዓላማ:**

ጌታ ለራሱ ክብር እና አካሉን ማለትም ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ልዩ ልዩ ጸጋዎችን ሠጥቶናል። ከእነዚህ ጸጋዎች አንዱ የነቢይነት ወይም የትንቢት ሥጦታ ነው። የዚህ ጥናት ዓላማ እግዚአብሔርን ስለ ሰጠን አገልጋዮች ለማመስገንና የሰጠንንም ነቢያትንና አገልግሎታቸውን አንዴት እግዚአብሔር በሚከብርብት እና ስዎች በሚታነፁብት መንገድ መጠቀም አንደምንችል ለማመልከት::

**መግቢያ:**

ነቢይ ማለት ከጌታ የተላከ ማለት ሲሆን ትንቢት ማለት ደግሞ ያለፈ፣ የቅርብ ወይም የሩቅን ነገር መግለጥ ማለት ነው። አስቀድሞ መናገር ማለትንም ያጠቃልላል። ነቢይ ወኪል ወይም የእግዛብሐኤር አፍ ነው። መፅሐፍ ቅዱስን በጥቅሉ ስናይ እግዚአብሔር የነቢይነትን ስጦታ ወይንም አገልግሎት በብሉይና በአዲስ ኪዳንም የሚጠቀምበት አግልግሎት አንደሆነ በጣም ግልፅ ነው:: እውነተኞችም ውሸተኞችም ነቢያት በእግዚአብሔር ሕዝብ መሃከል ይኖሩ እነደነበረ ከእግዚአብሔር ቃል እንማራለን (2ዜና 18:23፣ ኤር 27:10-16፣ ኤር 29:9-21):: በዚህም ምክንያት ሚዛኑን በጠበቀ ሁኔታ እንድንጠቀምበትም በዙ ማስጠንቀቂያ በእግዚአብሔር ቃል ተፅፏል:: ይሄም ማለት እግዚአብሔር ለዓላማ እና ለህዝቡ ጥቅም የሰጠውን ለመጠቀም ሳንፈራ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ሥር መሆኑን በመረዳት ለመመርመር ሳንፈራና ወደ ኋላ ሳንል አገልግሎቱን ማሳደግና ተጠቃሚ መሆን መቻል ማለት ነው:: ሰለዚህ በዚህ ጥናት የእግዚአብሔር ቃል በ1 ቆሮ 14:1 “መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢትን መናገርን በብርቱ ፈልጉ” ይላል:: በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር በቃሉ “ትንቢትን አትናቁ ሁሉን ፈትኑ” – “ፈትኑ” ብሎ ካዘዘን የእግዚአብሄርን ቃል ምክር ትተን “ሁሉን” ዝም

ብለን ብንቀበል መልካም አይሆንም:: በዚህም መሰረት ቅዱሳን ይሄንን ስጦታ እንዲፈልጉ ለማበረታትና አንደ እግዚአብሔር ቃል ለእግዚአብሔር ክብርም ሰውም የሚታነፅበት አገልግሎት እንዲሆን ለመማማር ነው::

የነቢያት አግልግሎት ዓላማው የጌታን ህዝብ ለማነፅ፣ ለመምክርና ለማጽናናት እና ሌሎችን ወደ ጌታ ለማምጣት እንደሆነ 1ቆሮ 14:3 ይነግረናል:: እንዲሁም የእግዚአብሔርን ህልውና ለመግለፅና ክብርን ለእርሱ ለማምጣት እንደሆነም በ1ቆሮ 14:24-25:: እንመለከታለን። እነዚህን ዓላማዎች በመረዳት በብርቱ አንድንፈልገው ተመክርናል (1 ቆሮ 14:1 ):: ነቢያቶች የሚያመጡት ትንቢት እንዲመረመር ፍቃደኞች እንዲሆኑ (1ቆሮ 14:29) አማኞችም ሁሉ ትንቢትን እንዲፈትኑ የእግዚአብሔር ቃል ያዛል (1 ተሰ 5:19-21):: ይህ ሁሉ ግን በትህትና በፍቅርና በመከባበር ነው።

**ትንቢቶችን ከምንፈትንባቸው መንገዶች መካከል -**

- በእግዚአብሔር ቃል 2ጢሞ 3:16- ከሁሉ የበላይና የእውነት መመዘኛው እርሱ ስለሆነ በቃሉ የተመሰረተ እንደሆነ መመዘን
- ቤተክርስቲያንን ያንፃል ወይ ብሎ መጠየቅ 1 ቆሮ 14:4
- ክርስቶስን ያከብራል ወይ መጠየቅ? ዮሐ 16:14
- እግዚአብሔርን እንድናመልክና እንድንፈራ ይረዳል ወይ ብሎ መመዘን? ዘዳ 13:1-5
- ነቢዩ የተናገረው ነገር ተፍፀሞል ወይ ብሎ መመርመር? ዘዳ 18:21- 22
- ነፃ ያወጣናል ወይስ የማስብና የመጠየቅ ነፃነታችንን ወስዶ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ሰዎችን እንድንፈራ ያደርግናል ብሎ መጠየቅ? ሮሜ 8:15-16
- እኛ ከተሞላንበት መንፈስ ጋርና ከሌሎች አማኞች መንፍስ ምስክርነት ይስማማል ወይ ብሎ መመዘን? 1 ዮሐንስ 2:27

## የመወያያ ጥያቄዎች

1) ነቢይ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚያሳይ አንድ አንድ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ አውጡ::
2) ነብይነት እንደስጦታ የተገለጸባቸውን ጥቅሶችን ከአዲስ ኪዳን ቢያንስ ሶስት ያህል አውጡ::
3) በ1 ቆሮ 14:3 መሰረት የነብይነት ስጦታ ለምን ይጠቅማል?
4) በ1 ቆሮ 14:24-25 መሰረት የነብይነት ስጦታ ለምን ይጠቅማል?
5) በ1 ቆሮ 14:1 "መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢትን መናገርን በብርቱ ፈልጉ" ሚለውን እንዴት እንረዳዋለን? አንድ ሰው ምን ሲያደርግ ነው በብርቱ ፈልጎል የሚባለው? በብርቱ እንዳንፈልግ ሊያደርጉን የሚችሉ ችግሮች አሉ ወይ? ካሉ እንዴት ነው ችግሮቹን አልፈን መሄድ የምንችለው? ይሄንን በብርቱ መፈለግስ በ1 ቆሮ 12:11 ካለው ጥቅስ ጋር እንዴት ነው ማመጣጠን (balance) ማድረግ የሚቻለው?
6) በአዲስ ኪዳን የነብያት አገልግሎትን በተመለከተ 1ቆሮ 14:29 "ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው፤" ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህንን መንፈሳዊ መሮሆ ሥራ ለማዋል ያለው ተግዳሮት ምንድነው?
7) ከ1ተሰ 5:19-21 ምን ያስተምረናል? ይሄ ማለት እውነተኛ ነቢያትም ሊሳሳቱ ይችላሉ ማለት ነው ወይስ አንድ ነቢይ እውነተኛ ከሆነ ሊሳሳት አይችልም ማለት ነው?

    "አትናቁ" "ሁሉን ፈትኑ" "መልካሙን ያዙ" የሚሉትን ሐሳቦች ለምን መጥቀስ እንደፈለገ ተወያዩ::

8) እስካሁን እንዳየነው እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት አንድ ነቢይ ነኝ የሚል ሰው ያመጣው መልክት እንዲፈተን ምን ያህል ፍቃደኛ መሆን ያለበት ይመስልሃል? ምንስ አይነት ባህርይ ይጠይቃል?

**<u>የውይይት ጥያቄዎች ካላለቁ ወደ ሚቀጥለው ሳምንት ማሻጋገር ትችላለችሁ</u>**

1- ሀሰተኞች ስላሉ እውነተኞች የሉም ማለት ነው? ካሉ እንዴት እናውቃለን?

2- አንድ ነቢይ ያመጣውን መልክት ለመፈትን የሚከተሉት ጥቅሶች ምን አይነት መመሪያ ይሰጣሉ? በእያንዳንዱ ጥቅስ መሰረት በአጭር ቃል ከትንቢት ምን እንደሚጠበቅ ተናገር::

ሀ- 2ጢሞ 3:16

ለ- 1 ቆሮ 14:4

ሐ- ዮሐ 16:14

መ- ዘዳ 13:1-5

ሠ- ዘዳ 18:21- 22

ረ- ሮሜ 8:15-16

ሰ- 1 ዮሐንስ 2:27

3- የሚከትሉትንና የተለያዩ መለክቶችን እንደምሳሌ በመውሰድ እስካሁን ባጠናነው መመሪያዎች መሰረት ተወያዩባችው::

ሀ- አንድ ሰው ተፈውስሃል የሚል መልዕክት ቢመጣለት ምንድ ነው ማድረግ አለበት? ያ ሰው ተፈውሶ ኑሮውን በሰላምና በጤና ሲኖር ማየት በሌሎች ሰዎች ላይ ምን ውጤት ወይንም ተፅኖ አለው?

ለ- ይሄ ተፈውሰሃል የተባለው ሰው ለረጅም ጊዜ ለውጥ ባያይ ምንድ ነው መደረግ ያለብት?

ሐ- ይሄ ተፈውሰሃል የተባለው ሰው በመጨረሻ ሳይፈወስ ህይወቱ ቢያልፍ ስለትንቢትና ስለነቢያት በሕዝብ አመለካከት ውስጥ ምን

ይፈጥራል? ይሄ ያልሆነ ተስፋን መስጠት በሰው ሕይወት ውስጥ ምን ተጽኖ አለው?

መ- ባየነው ምሳሌ መሰርት ነበያት አግልግሎታቸው ለእግዚአብሔር ክብር የሚያመጣና ሰውን የሚጠቅም አንዲሆን ምን ያህል መጠንቀቅ አለባቸው ትላለህ?

4- የእግዚአብሔር ቃል በ1 ቆሮ 14:1 “መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ” ብሎ በሚመክረን መሰረት ይህ አግልግሎት በመካከላችን አንድያድግ ምን ያህል አርስ በአርስ መበረታታት እና መፀለይ  አንዳለብን ተመመካከሩ::

ተባረኩ